የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት

አዘጋጅ፡-

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት

ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት

መስከረም 2006

መታሰቢነቱ



ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ (1932-1982ዓ.ም.)

መቅድም፡-

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እንደምናገኘው ስለወጣቶች ጎብረት(ማኅበር) የመጀመርያ ጽንሰ ሐሳብ የተነሳው ከግብጽ ከመጡ አባቶች በብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ዘመነ ፕርትክና ነው፡፡ የኢትዮጲያ ኦርቶዶስክ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ምዕመናንን በሃይማኖት በምግባር ለማድናት ካላት ጽኑ ዓላማ የተነሳ የሰንበት ት/ቤቶችን በየአጥቢያው አቢያተ ክርስቲያናት በማደራጀት የፍሬው ተቋዳሾች እንድንሆን ግንባር ቀደም አስተዋጽዎን አበርክታለች፡፡ ጉዞዋ የማይቋረጥ የሕይወት ስንቅን ያነገበ ነውና ዛሬም ወደፊትም ይህ ተግባርዋ ቀጣይነት ባለው መልኩ እንደ ሰንሰለት በተጣመረ የሰንበት ት/ቤቶች የእለት ከትትል ታግዞ ይራመዳል፡፡

ሰንበት ትምህርት ቤታችን በ1959 ዓ.ም ተመስርቶ እስካለንበት ዘመን አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡ በቅድምያ የመንፈሳዊ ወጣቶች ጎብረት የነበረ ቢሆንም 1986 ዓ.ም ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ትምህርት ቤት ተብሎ ተሰይሟል፡፡ ይህ ሰንበት ትምህርት ቤትም ወጣቶችን በመሰብሰብ ሥርዓተ ትምህርት ቀርጾ ኖት አዘጋጅቶ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዶግማ ቀኖና ትውፊት በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ይህንን መማርያ ኖት በተለያየ ወቅት በማዘጋጀት አዲስ ሥርዓተ ትምህርት በመቅረጽ አስታየት በመስጠት ትምህርት ክፍሉን በመምራት የተባበሩንን መምህራን ሙሉዓለም ሽፈራው ሙሉቀን ተሾመ ዮሐንስ ኃይሉ ዮሐንስ ገ/መስቀል ሚሊዮን ዳንኤል ጋዙ ሚኪያስ ይልማ ኢየሩሳሌም ጌቱ ዲ/ን ያሬድ መለሰ አብርሐም በቀለ እግዚአብሔር ጸጋውን ያድልልን እንላለን፡፡

ትምህርትና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል

መስከረም 2006 ዓ.ም

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

መግቢያ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ቃል “መጽሐፍ” እና “ቅዱስ” ከሚሉት ሁለት ቃላት የተገኘ ሲሆን “መጽሐፍ” የሚ ለው ቃል በአንድ ጥራዝ ውስጥ ተጠቃሎ የተሰበሰበ ጽሑፍ ማለት ሲሆን “ቅዱስ” የሚለው ቃል ደግሞ በግእዙ የተለየ፣ የከበረ የሚል ትርጉም ይሰጣል፡፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በአንድ ጥራዝ ውስጥ የተሰበሰበ የተለየ የተከበረ ጽሑፍ ማ ለት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ ?

1. አስገኝው እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ
   - ዘሌ 19፡2 “እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ”
2. ሰውን ወደ ቅድስና የሚያደርስ ስለ ሆነ
   - ራዕ 2፡7 “የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብጹዕ ነው”
3. በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሳን ሰዎች ስለጻፉት
   - 2ጴጥ 1፡20-21 “
4. የሰው ልጆች ከመፈጠራቸው በፊት ስላለው ነገርና ወደ ፊት ስለሚሆነው ነገር በእርግጠኝነት ስለሚናገር
   - ዘፍ 1፡1 “እግዚአብሔር በመጀመርያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ”
5. የሚያነቡትንና የሚሰሙትን ስለሚባርክ
   - ራዕ 1፡3
6. ዘመን የማይሽረው ስለሆነ
   - 1ጴ 1፡25 “የጌታ ቃል ለዘላለም ይኖራል”
7. ክብረ ቅዱሳንን የሚዘክር ስለሆነ

መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው?

መጽሐፍ ቅዱስን ብዛታቸው ከአርባ በላይ የሆኑ እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች ናቸው የጻፉት

- ኤር 36፡2 “አንድ የመጽሐፍ ክርታስ ውሰድ ለአንተም ከተናገርኩበት ቀን ከኢዮስያስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለእስራኤልና በይሁዳ ላይ በአሕዛብ ሁሉ ላይ የተናገርኩትን ቃል ሁሉ ጻፍበት”
- 2ጴጥ 1፡20-21 “በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ”

መጽሐፍ ቅዱስ መቼ እና የት ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ሰዎች እንደተጻፈ ሁሉ የተጻፈበት ዘመንና ቦታም እንዲሁ የተለያየ ነው፡፡ የመጀመርያው መጽሐፍ መጽሐፈ ሄኖክ ከተጻፈበት ከ1486 ዓ/ዓ ጀምሮ የመጨረሻው መጽሐፍ ዮሐንስ ራዕይ እስከተጻፈበት እስከ 98

ዓ/ም ድረስ ብዙ ዘመናት አልፈዋል፡፡ ጸሐፊዎቹም በተለያየ ቦታ በተለያየ ሥራ ይተዳደሩ የነበሩ ሰዎች በተለያየ ዘመን ጽፈውታል፡፡

- ለምሳሌ እነ ቅዱስ ጴጥሮስ ከዓሣ አጥማጅነት፣እነ ነቢዩ አሞጽ ከግብርና ሥራ ወዘተ.... ተጠርተው ጽፈውታል፡፡
- የተጻፉበትንም ቦታ የጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል፡-

የመጽሐፉ ስም	የተጻፈበት ቦታ
❖ የኦሪት መጽሐፍት	በሲና ምድረ በዳ
❖ መጽሐፈ ኢያሱ	በምድረ ከነዓን(እስራኤል)
❖ መጽሐፈ አስቴር	በፋርስ
❖ ትንቢተ ዳንኤል	በባቢሎን
❖ ዮሐንስ ራዕይ	በፍጥሞ ደሴት

መጽሐፍ ቅዱስ በምን ቋንቋ ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቅዱሳን ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ቋንቋዎች ነው የተጻፈው፡፡ ለምሳሌ ያህል አብዛኞቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በእብራይስጥ ሲሆን ትንቢተ ዳንኤል በአረማይክ ቋንቋ ነው፡፡ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ በአብዛኞቹ በጽርዕ(ግሪክ) ቋንቋ ሲጻፉ የማቴዎስ ወንጌል በእብራይስጥ የማርቆስ ወንጌል በሮማይስጥ ቋንቋ ተጽፎዋል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች

- የቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጎም እግዚአብሔርንና ፈቃዱን ወይም ትእዛዙን ለማወቅ ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጎዋል፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመርያ ጊዜ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ980 አካባቢ ወደ ግእዝ ተተርጉሞዋል፡፡በእርግጥም በአለም አቀፍ ደረጃ በደንብ የሚታወቀው ለመጀመርያ ጊዜ በ280 (ቅ/ል/ክ) አካባቢ በንጉሥ በጥሊሞስ ወደ ግሪክ መተርጎሙን ነው፡፡ ይህ ትርጉም የሰባው ሊቃውንት (ሊቃናት) ትርጉም ነው፡፡ ይህን ትርጉም ለማቅናት በ2 መ/ክ/ዘ ሲማኩስ፣አኪላና በ3 መ/ክ/ዘ ደግሞ ሉቅያኖስ ተነሥቶ ነበር፡፡
- በ4ኛው መ/ክ/ዘ ደግሞ አባታችን አባ ጀሮም ለ40 ዓመታት የእብራይስጥን ቋንቋ በማጥናት ቩልጌት ተርጉሞታል፡፡ከቩልጌት ወደ ላቲን ቋንቋ ብሉም ወደ ጎቲክ(ጀርመን) ተተርጉሟል፡፡
- ሶርያም የሱርስት ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉማለች፡፡በዚህም አባ ራሉላ፣አባ ፊልክስዮስ ይጠቀሳሉ፡፡
- በአርመንም ቅዱስ ሚስሮኝና ቅዱስ ሳህክ ትርጉሞችን አቅንተዋል፡፡
- ከዚህ ሁሉ ሂደት በኋላ ዛሬ በዓለም ላይ ከ2ሺ 123 በላይ ትርጉሞች ይገኛሉ፡፡

ቀኖናተ መጽሐፍ ቅዱስ(የመጽሐፍ ቅዱስ ቀኖና/ቁጥር/)

- ይህ ቀኖና ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን ያያይዛል፡፡መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሲሆን የተለያዩ መጻሕፍትን በውስጡ የያዘ ነው፡፡እነዚህ የመጻሕፍት ክፍሎች በአንድ ወቅት ተጽፈው የተዘጋጁ ሳይሆኑ በተለያየ ዘመንና ጊዜ በተለያዩ ጸሐፍት ተጽፈው የተጠረዙ ናቸው፡፡በመጀመርያ በብራና ይጻፉ ነበር፡፡(2ጢሞ 4፡3)፣(ሐዋ 8፡28)፣(ሉቃ 4፡17-20)

- መጽሐፍትን መሰብሰብና ማዘጋጀት የተጀመረው ከመጀመርያው መ/ክ/ዘ ጀምሮ ነው::ለዚህም 8ተኛው የሐዋርያት ድንጋጌ ስለመጽሐፍ ቅዱስ የሚያወራ ነው::
- ከዚህም ሌላ በ325ዓ/ም በኒቂያ በተካሄደው ጉባዔ ላይ እውነተኞቹን ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመሰብሰብ በተወሰነው መሠረት ቅዱስ አትናቴዎስ ሐዋርያዊ በ367 ዓ/ም በ39ኛው የትንሣኤ መልዕክቱ ላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቁጥርና ዓይነት አስታውቋል፤ ይህም 46ቱን የብሉይ ኪዳንንና 35ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን የያዘ ነው::
- ላቲኖች 73ቱን፣ግሪካውያን 76ቱን መጻሕፍት ይቀበላሉ::አርቶዶክስ ተዋሕዶ በብዛት ከሚታቁት 27ቱ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በተለየ ለምግባር የሚረዱትን 8ቱን የሥርዓት መጻሕፍት በሲኖዶስ ወስና ትቀበላለች::መጻሕፍቱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከእርገቱ አስቀድሞ የሠራውን የሃይማኖት የሥርዓት ትምህርት የያዘና በሐዋርያትና በቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር በቅዱስ ቀሌምንጦስ የተጻፉ ናቸው::

የኢትዮጲያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቀኖና ምናጮች

- ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 2
- ሥርዓተ ጽዮን (የሐዋርያት ቀኖና)
- ቀሌምንጦስ ቀዳማዊ (ረስጠአ 82፣83)
- ረስጠብ (74 ቀኖናት)
- ረስጠጅ (ቀሌምንጦስ ሣልስ፣56 ቀኖናት)
- የግሪክ ሐዲስ ኪዳን የእጅ መዝገብ (ኮዴክስ)
- የቫቲካንና የእስክንድርያ ኮዴክስ
- ጥንታዊያን ትርጉሞች:-የሱርስት፣የላቲን፣የአርመን ትርጉሞች

ፕሮቴስታንቶችና አይሁድ የማይቀበሏቸው 15 መጻሕፍት

- ለቁጥሩ መለያ መሠረታዊ ምክንያት
  - የአይሁድ ምክንያት:-
    - በ90 ዓ/ም በጃሚ ጉባዔ መጻሕፍቱን ላለመቀበል ወሰኑ ምክንያታቸውም ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግልጽ በመናገራቸው ነው::(ዕዝ 4:1)፣(ሲራ 24:10)
    - በግሪክ ቋንቋ የተጻፉትን ለግሪኮች ካላቸው ጥላቻ አንጻር
    - መጽሐፈ ሄኖክና መጽሐፈ ኩፋሌ በወቅቱ በመጥፋታቸው ነው::
  - የፕሮቴስታንቶች ምክንያት
    - ከካቶሊኮች ጋር የነበራቸው ጥላቻ ብዙዎቹን አልተቀበሉም
    - የአይሁዶችን ውሳኔ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በመቀበል
    - ጸሐፊዎቹንና የመጽሐፉን ምንጭ ካለመቀበል

ለምሳሌ:- መጽሐፈ መቃብያን፣መጽሐፈ ሲራክ

- ረዕይ 22 ላይ ያለውን በመጥቀስ

ሐተታ፡-ይህ ቃል የተጠቀሰው ተለይቶ የተጠቀሰው ለዮሐንስ ራዕይ መጽሐፍ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ቃሉ ከ15ቱ መጻሕፍት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ምክንያቱም ተጨማሪ መጻሕፍት ስላልሆኑ ነው፡፡ ተጨማሪ የተባሉበት ምክንያት አይሁድ ስለማይቀበሏቸው ነው፡፡

ይህንን ቃል የጻፈው ዮሐንስ አፈወርቅ ሲሆን ዮሐንስ ራዕይ ጠፍቶ ስለነበር ለአርሱ በድጋሚ ተገልጾለት ስለጻፈው ይህንን ቃል ጽፍታል፡፡ ይልቅ ቃሉ እነርሱን ያነደለ ከቅድስቲቱ ከተማ እድል ፈንታ የላቸሁም ይላቸዋል፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ጥቅም

- እግዚአብሔርን የበለጠ ለማወቅና ለመቀደስ (ዮሐ 17፡17)፣(ኤፌ 5፡26)
- ክፉንና በጎውን ለመለየት (መዝ 118፡105)
- እውነትን ለማወቅ (ምሳ 22፡19-20)
- መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ (ያዕ 1፡25)
- መንፈሳዊ ውጊያን ለመዋጋት (ኤፌ 6፡10-18)

እግዚአብሔር ለምን በመጻሕፍት ተናገረ?

እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በራዕይ፣በሕልምና በመልአክ በሌላም አስተርእዮ ለሕዝቡ ተናግሯል፤በኋላም ጌታችን ፊት ለፊት ቃል በቃል ተናግሯል፡፡ (ማቴ 5፡1) “አፉን ከፍቶ አስተማራቸው” እንዲል፡፡ዛሬ ደግሞ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይናገር ዘንድ ድምጹን የሚሰማበትን መጽሐፍትን ሰጠን፡፡(መዝ 86፡6) “እግዚአብሔር ለሕዝቡ በውስጥዋ ለተወለዱት አለቆች በመጽሐፍ ነግሯቸዋል”፣ (ዮሐ 5፡39) “መጻሕፍትን መርምሩ ታገኛላችሁ” እንደተባለ

ከዚህም ሌላ፡-

- ያላመኑትን ለማሳመን (ማር 16፡16)፣(ሐዋ 10፡1፣2፡36)
- ያልተመለሱትን ለመመለስ (ዘካ1፡13)፣(ሉቃ 15፡7)፣(ሕዝ18፡30)፣(ማቴ3፡1-2)፣(ኢሳ 30፡15)
- ያልጸኑትን በምግባር በሃይማኖት ለማጽናት(ዕብ4፡4)፣(2ጢሞ4፡2)፣(ያዕ 1፡12)፣(ማቴ24፡13)

መጽሐፍ ቅዱስና ኢትዮጲያ

በብሉይ ኪዳንም ሆነ በሐዲስ ኪዳን ሀገራችን ኢትዮጲያ በቅዱሳት መጻህፍት ትልቅ ስፍራ አላት ሁለቱንም በመቀበል ብቸኛ ናትና ከጥንት ጀምሮ መጽሐፍትን ለሀገራችን ይታወቅ ነበር 1ኛ ነገ 10-1-3፣2ኛዜና 9-12 ሐዋ 8-26 ተመልከት ከግእዝ ትርጉም በኃላ በአባ አብርሃም ወደ አማርኛ ተተርጉሞዋል፡፡ በአለቃ ተወልደ መድኅን ወደ ትግርኛ በአናሲሞስ ነሲቡ ወደ ኦሮምኛ ዛሬ በጠቅላላ ወደ 3 የሀገራችን ቋንቋዎች ተተርጉሟል፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘትና ዝርዝር

መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተብሎ በሁለት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. ብሉይ ኪዳን፡- የቃሉ ትርጉም የጥንት፣የቆየ፣የመጀመርያ ውል ስምምነት ማለት ነው፡፡ ከጌታ ልደት በፊት የነበረውን ዘመን በአጠቃላይ ይይዛል፡፡ በዚህም እግዚአብሔር ከአዳም ጋር የገባውን ቃልኪዳን (ዘፍ

2፡16)፣ ከቅዱሳን አባቶቻችን ጋር የገባውን ቃልኪዳን በአጠቃላይ ያካትታል፡፡(መዝ 88፡3) በዚህ ዘመን የተጻፉት መጻሕፍት 46 ሲሆኑ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ፡፡

2. ሐዲስ ኪዳን፡- የቃሉ ትርጉም አዲስ ውል ስምምነት ማለት ሲሆን እግዚአብሔር ወዶ ፈቅዶ ባናገረው ትንቢት መሠረት (ኤር 31፡31)፣(ዳን 24፡27) የፍቅር አምላክ በማይመረመር ጥበቡ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ያደረገውን የሰው ልጆች የማዳን ጉዞና ከእስራኤል ዘነፍስ (ከክርስቲያኖች) ጋር ያደረገውን የውል ስምምነት ያመለክታል፡፡ (ማቴ 26፡26)፣(ዮሐ53፡59)፣(1ኛቆሮ 11፡23-26) በዚህ ዘመን የተጻፉትን መጻሕፍት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በመባል ይታወቃሉ፣በቁጥርም 35 ናቸው፡፡

ምዕራፍ ሁለት

የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

አርባ ስድስቱን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በአጠቃላይ በአራት ከፍለን እንመለከታቸዋለን፡፡

1. የሕግ(የኦሪት) ክፍል መጻሕፍት
2. የታሪክ ክፍል መጻሕፍት
3. የትምህርት ክፍል መጻሕፍት
4. የመዝሙርና የጥበብ ክፍል መጻሕፍት
5. የትንቢት ክፍል መጻሕፍት

➢ መጻሕፍቱን ከዚህ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታቸዋለን

1. የሕግ(የኦሪት) ክፍል መጻሕፍት

ኦሪት፡- የሚለው ቃል የሱርስት(የጥንት ሶርያ) ቃል ሲሆን ሕግ ማለት ነው፡፡ በእብራይስጥ ቶራ በግሪክ ኖመስ ይባላል፡፡ትርጉሙም ብርሃን ማለት ነው፡፡

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከአስራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ከነገደ ሌዊ የተወለደ ሲሆን የስሙ ትርጉም ከውሃ የተገኘ ማለት ነው፤አባቱ እንበረም እናቱ ዮካብድ ይባላሉ፡፡(ዘጸ 1፡2፡ እና 3) በዚህ መጻሕፍት ክፍል እንደተገለተው በእስራኤል የመከራ ዘመን በፈርኦን ቤተ መንግሥት ለማደግ እንደበቃ በኋላም ከፈርኦን ቤት ተድላ ድስታ የእስራኤልን የተስፋ መከራ በመምረጥ ፈርኦንን ትቶ በምድያም ምድር ተቀመጠ፡፡(ዕብ 11፡4)

በመጨረሻም በሲና በረሃ እግዚአብሔር ተገልጦለት ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ ያወጣ ታላቅ አባት ነው፡፡ ከዚህም በኋላ እስራኤልን አርባ ዓመት ያህል በምድረ በዳ የመራ ሲሆን በመጨረሻም በ120 ዘመኑ አርፎ በናባው ተራራ ተቀብሯል፡፡

በዚህ ክፍል የሚታወቁት መጻሕፍት በቁጥር አምስት ሲሆኑ እነዚህ መጻሕፍት በዚህ ክፍል የተመደቡት ካላቸው የይዘት አቀራረብ፣ከተጻፉበት ዘመንና ከጸሐፊው አንጻር ነው፡፡ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሲና ተራራ እነዚህን መጻሕፍት በ1500 ዓ.ዓ በእብራይስጥ ቋንቋ ጽፎዋቸዋል፡፡

ሀ. ኦሪት ዘልደት/ ኦሪት ዘፍጥረት/

ዘፍጥረት ወይም ዘልደት ማለት ግኝት ፣ካለመኖር ወደ መኖር መምጣት ማለት ነው፡፡ መጽሐፉ የሥነ ፍጥረትን አጀማመርና አመጣጥን የሚያትት በመሆኑ ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት ሊቀ ነብያት ሙሴ በ1500 ዓ.ዓ.ቅ.ል. ክርስቶስ በሲና ምድረ በዳ ተጽፏል፡፡ 50 ያህል ምዕራፎችም አሉት፡፡

የመጽሐፉ ይዘት፡-

ስለ ሥነ ፍጥረት አጀማመር ስለ አርዕስተ አበው ስለ ሰው ልጆች በደልና ቅጣት እንዲሁም ስለ አብርሃም ዘሮች ይተርካል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-5)፡- ስለ ሥነ ፍጥረት ስለ ሰው ልጅ ውድቀትና የመጀመሪያ አባቶች እድሜ
2. (ከምዕ 6-11)፡- የሰው ልጆች በጎጢአታቸው የደረሰባቸው ቅጣትና ስለ ባቢሎን ግንብ ይተርካል፡፡
3. (ከም **12-26**)፡- የአብርሃም የሃይማኖት ጉዞ ፡ ስለ ሰዶምና ገሞራ ጥፋት ፡ የይስሐቅን ታሪክ ይተርካል፡፡
4. **(ከምዕ 27-50)**፡- የያዕቆብና የዮሴፍ ታሪክን፣ የእስራኤልን ወደግብጽ መውረድ ይተርካል፡፡

ለ.ኦሪት ዘጸአት

ዘጸአት ማለት በግእዙ መውጣት ማለት ሲሆን እስራኤላውያን ከግብጽ ስለመውጣታቸው ይናገራልና፡፡ ጸሐፊው ሙሴ ሲሆን በደብረ ሲና **1500** ዓ.ዓ እንደተጻፈ ይታመናል፡፡ ኦሪት ዘጸአት **40** ምዕራፎችና ያካተተ መጽሐፍ ነው፡፡ ፡

የመጽሐፉ ይዘት፡-

የእስራኤል ሕዝብ በሙሴ መሪነት ከግብጽ ባርነት መውጣታቸውን በሰፊው ይተርካል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-4)፡- የሙሴ ታሪክ ከልደቱ እስከ መጠራቱ
2. (ከምዕ 5-11)፡- በግብፅ ላይ ስለወረዱት መቅሰፍቶች
3. (ከምዕ 12-15)፡- እስራኤላውያን የኤርትራን ባሕር ስለመሻገራቸው
4. (ከምዕ 16-40)፡- እስራኤላውያን መና እንደወረደላቸው የሙሴን ሕግ መቀበልን እንዲሁም እስራኤላውያን ጣኦት በማምለካቸው ስለተቀጡት ቅጣት ይናገራል፡፡

ሐ. ኦሪት ዘሌዋውያን

ዘሌዋውያን ማለት የሌዋውያን ማለት ነው፡፡ ሌዊ የያዕቆብ ልጅ ስም ሲሆን የሌዊ ልጆች (ትውልድ) ለእስራኤል ሕዝብ በክህነት እንዲያገለግሉ የተመረጡ ስለሆነ የእነዚህን የካህናት ሥርዓት በዝርዝር ስለሚያስረዳ ይህ ስያሜ መጽሐፉ ተሰጥቶታል፡፡ መፅሐፉ 27 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ሊቀ ነቢያት ሙሴ በሲና ተራራ ላይ በ1508 ዓ.ዓ እንደጻፈው ይታመናል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ ሥርዓተ ክህነት፣ ስለመሥዋዕቶች፣ ስለ በዓላት፣ ስለምግቦች ወዘተ ይናገራል፡፡

አከፋፈሉ፡-

6. (ከምዕ 1-10)፡- ስለ መሥዋዕትና ስለ ሥርዓተ ክህነት
7. (ከምዕ 11-16)፡- ስለ መባልዕትና የማንጻት ሥርዓት
8. (ከምዕ 17-22)፡- ስለ ጋብቻ እና የክህነት ምርጫ
9. (ከምዕ 23-27)፡- ስለ ሕግጋተ እግዚአብሔርና በዓላተ እስራኤል ያወራል፡፡

መ. ኦሪት ዘኁልቁ

ኁልቁ' በግእዝ ቋንቋ ቁጥር ማለት ነው፡፡ እስራኤላውያን እግዚአብሔር ለሙሴ ባዘዘው መሠረት ስለመቆጠራቸው የሚተርክ መጽሐፍ በመሆኑ ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡ ይህ መፅሐፍ 36 ምዕራፎች ያሉት በሙሴ የተጻፈ ሲሆን የተጻፈበት ቦታም በሲና ተራራ ላይ በ1500 ዓ.ዓ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

እስራኤላውያን ሁለት ጊዜ ስለመቆጠራቸው በግብጽ የወጡት የእስራኤላውያን ስም ዝርዝር እና በበደላቸው መቀጣታቸውን ይገልፃል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-10)፡- በሲና ሰፍረው ሳሉ የሕዝቡ ቆጠራ መጀመሩ፣ ለጉዞ መዘጋጀታቸውን እና ወደ ዮርዳኖስ ያደረጉትን ጉዞ ይዟል፡፡
2. (ከምዕ 11-12)፡- በሲና ተራራ እስከ ቃዴስ በረሃ ድረስ ያደረጉትን ጉዞ
3. (ከምዕ 13-25)፡- ባለመታዘዛቸው በምድረ በዳ 40 ዘመን መንከራተታቸውን
4. (ከምዕ 26-36)፡- ከነዓን ለመግባት መዘጋጀታቸውን እና ከገቡ በኋላ ስለ መሬት ክፍፍል ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡

ሠ. ኦሪት ዘዳግም

ዘዳግም ማለት በግእዙ የተደገመ ማለት ነው፡፡ ከላይ ባሉት የኦሪት መጽሐፍት የተጻፉትን ዋና ዋና ኃይለ ቃሎች በስብከት መልክ ስለሚደግም መጽሐፉ እንዲህ ሊባል ችሏል፡፡ ሙሴ በዮርዳኖስ ምድር ባለችው በሞአብ ሀገር ለእስራኤል ሕዝብ የተናገረውን የያዘና 34 ምዕራፍ ያሉት መጽሐፍ ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ሙሴ ሲሆን ቅ.ል.ክ. በ1500 ዓ.ዓ በሲና ተራራ ላይ ጽፎታል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ከዘጸአት ጀምሮ ያሉትን መጻሕፍት በስብከት መልክ መድገም

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 11-11)፡- ያለፈውን እንዳያስታውሱ ማሳሰቢያ
2. (ከምዕ 12-26)፡- አዳዲስ ሕግጋትን ኦሪትን እንዲጠብቁ
3. (ከምዕ 27-34)፡- ወደፊት እንዳይበድሉ ማስጠንቀቂያ የሙሴን ዕረፍትና የኢያሱን መሾም ይናገራል፡፡

2.የታሪክ ክፍል መጻሕፍት

የብሉይ ኪዳን የታሪክ መጻሕፍት ብዛታቸው አስራ ሰባት ነው። እነዚህ መጽሐፍ የእስራኤልን ነገሥታትና ሕዝብ ታሪክ የሚናገሩ ናቸው።

ሀ. መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ

ኢያሱ የቀድሞ ስሙ አውሴን ይባል ነበር። ኢያሱ ብሎ ስም ያወጣለት ሊቀ ነብያት ሙሴ ነው። ኢያሱ ማለት እግዚአብሔር አዳኝ ነው ማለት ነው። አባቱ ነዌ ይባላል ከሙሴ በኋላ ሕዝበ እስራኤልን እየመራ ምድረ ርስት ከነዓንን ያወረሳቸው ሲሆን ሙሴ ከላካቸው ሰላዮች መካከል አንዱ ነበር። በ120 ዓመቱም አርፏል።

መጽሐፉን የጻፈው ኢያሱ ሲሆን የተጻፈበት ዘመን ከ1400-1300 ቅ.ል.ክ ነው። 24 ምዕራፎች ያሉት በኢየሩሳሌም የተጻፈ የታሪክ መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፈ ኢያሱ ሕዝበ እስራኤል በእግዚአብሔር ኃይልና በኢያሱ መሪነት ከነዓን እንደገቡ ይናገራል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-12)፡- የእስራኤልን ከነዓን መግባት
2. (ከምዕ 13-22)፡- ምድርን ርስትን መከፋፈላቸውን
3. (ከምዕ 23-24)፡- የኢያሱ የመጨረሻ ምክርና ስንብት ተጽፏል።

ለ. መጽሐፈ መሳፍንት

መስፍን ማለት ፈራጅ፤ አስተዳዳሪ ማለት ነው። መጽሐፉ ከኢያሱ ሞት በኃላ ለ2400 ዓመታት ያህል እስራኤልን ስላስተዳደሩ መሳፍንት የሚተርክ በመሆኑ ይህ ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህ መጽሐፍ ነቢዩ ሳሙኤል እንደጻፈው የሚታመን 21 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው። የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ በምድረ እስራኤል ከ1070-1017 ዓ.ዓ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

በእስራኤል ንጉሥ ባልነበረበት ዘመን እግዚአብሔር አምላክ መሳፍንትን እያስነሣ እንዴት ከጠላት እጅ ያድናት እንደነበረ ይተርካል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-2)፡- እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ውለታ ስለመዘንጋታቸው
2. (ከምዕ 3-16)፡- ስለመሳፍንቱ አነሣስና በእነርሱ አማካኝነት ስለተፈጸሙ ታሪኮች
3. (ከምዕ 17-21)፡- መሳፍንቱ ባልነበሩበት ዘመን ስለተፈጸሙ ታሪኮች ይገልጻል።

ሐ. መጽሐፈ ሩት

ሩት ማለት መልክ፣ ውበት፣ ቆንጆ፣ ወዳጅ፣ ጓደኛ ማለት ነው። መጽሐፉ ስለ ሩት ስለሚተርክ በዚህ ስም ተጠርቷል። ሩት ሞአባዊት ሴት ስትሆን በእስራኤል ረኃብ በተነሣ ጊዜ አቤሜሌክ የተባለ ሰው ኑዓሚን ከተባለች ሚስቱ እና ከሁለት ወንድ ልጆቹ ጋር ወደ ሞአብ ተሰድዶ በዚያው አርፏል። ከሁለቱ ወንድ ልጆች መካከል አንደኛው ሩትን አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞቷል። ኑዓሚን ወደ ሀገሯ ስትመለስ ሩትም አብራት ተመልሳ ቦዔዝ የተባለ ሰው አግብታ ኢዮቤድ የተባለውን የዳዊትን አያት ወልዳለች። ይህች ሴት ከአሕዛብ ወገን ስትሆን ታሪኳ የተጻፈው በእምነቷና በደግነቷ እንዲሁም የዳዊት ቅድመ አያት ሆና በጌታ የትውልድ ሐረግ ውስጥ በመግባቷ ነው።

መጽሐፉ 4 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን ሳሙኤል በ1100 ዓ.ዓ. በእስራኤል ምድር እንደጻፈው ይታመናል።

የመጽሐፉ ይዘት፡- አንዲት ሩት ስለተባለች ደግ ሴት ይተርካል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ምዕ-1)፡- ሩት ከኑዓሚን ጋር ወደ ቤተልሔም እንደሄደች
2. (ምዕ-2)፡- ሩት ከአቤሜሌክ ዘመድ ከቦኤዝ እርሻ እንደቃረመች
3. (ምዕ-3)፡- ሩት ቦኤዝ እንዲያገባት ያደረገችውን ጥበብና ጥረት
4. (ምዕ-4)፡- ሩት ቦኤዝን አግብታ የዳዊትን አያት ኢዮቤድን እንደወለደች

መጽሐፈ ሳሙኤል

ሳሙኤል ማለት እግዚአብሔርን ሰማኝ ማለት ነው። አባቱ ሕልቃና እናቱም ሃና ትባላለች።በእስራኤል ከተነሡት መሳፍንት የመጨረሻው ነው። ሳሙኤል እስራኤልን ለ20 ዓመታት መርቶ የመጀመሪያው የእስራኤል ንጉሥ ሳኦል ሲያነግሥ ዘመነ መሳፍንት አብቅቷል። ዳዊትን ቀብቶ ያነገሠው ይኸው ሳሙኤል ነው። መጽሐፉን ሰባው ሊቃውንት ከመተርጎማቸው በፊት መጽሐፈ ነገሥት ይባል ነበር።

መ. መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ

መጽሐፉ 3ት ምዕራፎችን የያዘ እና በሳሙኤል የተጻፈ ሲሆን የተጻፈበት ዘመንም 1075-975 ቅ.ል.ክ በኢየሩሳሌም ነው።

የመጽሐፉ ይዘት፡-ስለ ካህኑ ኤሊ ልጆች፣ ስለ ሳሙኤል፣ ስለ ሳኦል እና ዳዊት ይተርካል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-3)፡- የሳሙኤልን መነሣት እና የኤሊ ልጆችን ሥራ ይናገራል
2. (ከምዕ 4-6)፡- የታቦተ ጽዮን መማረክ እና በኤሊ ላይ ስለደረሰውን ነገር
3. (ከምዕ 7-31)፡-የሳሙኤልን ምስፍና እና የሳኦልና የዳዊትን ንግሥና ይገልጻል።

ሠ. መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ

ይህ መጽሐፍ ከመጀመሪያው መጽሐፍ የቀጠለ ታሪክን ይተርካል። መጽሐፉን ሳሙኤል ጀምሮት ናታንና ጋድ እንደጨረሱት ይናገራል። የተጻፈው በኢየሩሳሌም ከ1075-975 ዓ.ዓ ነው። መጽሐፉ 24 ምዕራፎች አሉት፡

የመጽሐፉ ይዘት

የዳዊትን ንግሥና ዘመን፣ ስለታቦተ ጽዮን፣ ስለዳዊት በደልና ንስሐ እና ያደረጋቸውን ጦርነቶች ይገልጽልናል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-5)፡- ስለ ዳዊት ንግሥና
2. (ከምዕ 6-7)፡- ስለታቦተ ጽዮን
3. (ከምዕ 8-20)፡- የነቢዩ ዳዊት በደልና ንስሐ
4. (ከምዕ 21-24)፡- ስለሦስቱ ዓመት ጽኑ ረሐብ ፣ዳዊት ሕዝቡን ማስቆጠሩ እና የእግዚአብሔርን ቁጣ ይገልፃል፡፡

ረ. መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ

ነገሥት ማለት ንጉሦች ማለት ነው፡፡ መጽሐፉ 22 ምዕራፎች ሲኖሩት የመጽሐፉ ጸሐፊ በእርግጠኝነት አይታወቅም፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ግምቶች አሉ፡፡ አንዳንዶች ጸሐፊው ኤርምያስ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ንጉሥ ሰለሞን እና ንጉሥ ሕዝቅያስ ናቸውም የሚሉ አሉ፡፡ የተጻፈበት ዘመን በ567 ዓ.ዓ በኢየሩሳሌም ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ ሰሎሞን፣ ስለ ቤተመቅደሱ መታነፅና እስራኤል ለ2 ስለመከፈላቸው የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-10)፡- ስለ ሰለሞን ንግሥና እና ስለቤተ መቅደሱ መታነጽ
2. (ከምዕ 11-12)፡- ስለእስራኤል ለሁለት መከፈል፣ ስለ ነገሡት ነገሥታት እና ስለ ነቢያት ይናገራል፡፡

ሰ. መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ

የተጻፈበት ዘመን እና ቦታው እንደ ነገሥት ቀዳማዊ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ከመጀመሪያው መጽሐፍ በመቀጠል ሁለቱ ነገሥታት በጠላት ተከበው ወደ ምርኮ እስከወረዱበት ያለውን ይገልፃል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-17)፡- ስለ ይሁዳና ስለእስራኤል መንግሥት በአሦር መንግሥት መማረክን ይተርካል፡፡
2. (ከምዕ 18-25)፡- ስለ ይሁዳ መንግሥት እስከ ናቡከደነጾር ምርኮ ያለውን ይገልፃል፡፡

ሸ. መጽሐፈ ዜና መዋዕለ ቀዳማዊ

የቃሉ ትርጉም የዕለት ዜና ማለት ነው፡፡ መጽሐፉ የተጻፈው ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ከክርስቶስ ልደት በፊት 450-300 ዓ.ዓ ባለው ጊዜ ውስጥ በካህኑ ዕዝራ አማካኝነት ነው፡፡መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 29 ምዕራፎችን የያዘ የታሪክ መጽሐፍ ሲሆን በኢየሩሳሌም ከምርኮ መልስ እንደተጻፈ ይታመናል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ከሳኦል ሞት ጀምሮ እስከ ቂሮስ አዋጅ ያለፈውን ታሪክ በቅደም ተከተል የቀደመውን ሃይማኖታዊ ፍሬ ነገር በድጋሚ ይገልጻል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-9)፡- የቀደመው የእስራኤል አባቶችን የትውልድ ሐረግ ይዘረዝራል
2. (ከምዕ 10-29)፡- የሳኦል መውደቅ፣ የዳዊትን ንግሥና እና ለልጁ ሰሎሞን ማስረከብ ድረስ ያለውን ታሪክ ይይዛል፡፡

ቀ. መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ

የተጻፈበት ቦታ ጸሐፊው እና ዘመኑ እንደመጀመሪያው ክፍል ነው፡፡ መጽሐፉ ከዜና

መዋዕል ቀዳማዊ የሚቀጥል 36 ምዕራፎችን የያዘ የታሪክ መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት:- የሰሎሞን ቤተመቅደስ መሠረትና የእስራኤልን የነገሥታት ታሪክ አካቷል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-9)፡- ሰሎሞን ቤተ-መቅደስ ስለማሳነጹ ጥበቡን ለማየት ስለመጣችው ንግሥተ ሳባ ይዘረዝራል፡፡
2. (ከምዕ 10-16)፡- ከሰሎሞን ዕረፍት በኋላ ልጁ ሮብዓም በነገሠ ጊዜ መንግሥቱ ለሁለት ስለመከፈሉ
3. (ከምዕ 16-21)፡- ኢዮሳፍም የአባቱን መንበር መረከቡ እና እግዚብሔርን በመከተሉ ጠላቶቹ መደምሰሳቸውን ይተርካል፡፡
4. (ከምዕ 22-36)፡- የነገሥታት ታሪክ እና የይሁዳ ሕዝብ ምርኮ

በ. ጸሎተ ምናሴ

የቃሉ ትርጉም ማስረሻ ማለት ነው፡፡ ምናሴ የንጉሥ ሕዝቅያስ ልጅ ሲሆን(2ኛነገ 20-1) ባእድ አምልኮን እየተከተለ እግዚአብሔርን በማስቆጣቱ የአሦር ንጉሥ ማርኮ ወደ ባቢሎን በወሰደው ጊዜ የጸለየው ጸሎት ነው፡፡ በኋላም እግዚአብሔር ልመናውን ሰምቶ ከምርኮ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለስ አደረገው፡፡ ሕዝቡንም እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ስለማዘዙ መጽሐፉ ይናገራል፡፡ (2ኛ ዜና 33፥11-20)

መጽሐፉ የተጻፈው ከ450-300 ዓ.ዓ በኢየሩሳሌም በካህኑ ዕዝራ አማካኝነት እንደሆነ ይታመናል መጽሐፉ 1 ምዕራፍ ብቻ ይዟል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት፡- (በ2ኛ ዜና 35፥18) ላይ ያለውን የምናሴን ጸሎት ይገልጻል።

አከፋፈሉ ፡-

1. (ከቁ 1-6)፡- የእግዚአብሔር መሐሪነትና ኃያልነት ይገልጻል።
2. (ከቁ 7-13)፡-ምናሴ ኃጢያቱን በማመኑ የተደረገለትን ይቅርታና ለእግዚአብሔር ያቀረበው ምስጋና ይዟል።

ማሳሰቢያ፡- ጸሎተ ምናሴ አቆጣጠሩ ከሁለተኛ ዜና መዋልዕ ጋር ነው። ምክንያቱም 2ኛ ዜና 33-18 ላይ ምናሴ ስለመጸለዩ ይናገራልና።

ተ. መጽሐፈ ዕዝራ

ዕዝራ ማለት ረድኤት ማለት ነው። ዕዝራ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ያሰባሰበ ታላቅ ነቢይ ነው። የመጽሐፉ ጸሐፊ ካህኑ ዕዝራ ሲሆን በ467 ዓ.ዓ ከስደት መልስ በኢየሩሳሌም እንደተጻፈ ይተርካል። መጽሐፉ 10 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

የእስራኤል ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ መልስ ቤተ መቅደሱን ስለመሥራታቸው ይናገራል።

አከፋፈሉ

1. (ከምዕ 1-2)፡- በዘሩባቤል አማካኝነት የተደረገውን የስደት መልስ ይናገራል
2. (ከምዕ 3-6)፡- አምልኮተ እግዚአብሔርን እንደገና መጀመራቸው
3. (ከምዕ 7-10)፡- በዕዝራ አማካኝነት የተደረገውን የስደት መልስ

ማሳሰቢያ፡- እንደ ሰማንያ አንዱ ቅዱሳት መጻሕፍት አቆጣጠር መጽሐፈ ዕዝራ ከመጽሐፈ ነህምያ ጋር በመጣመር ይቆጠራል።

ቸ. መጽሐፈ ነህምያ

ነህምያ ማለት እግዚአብሔር አጽናኝ (አዳኝ) ነው ማለት ነው። ነህምያ የፋርስ ንጉሥ ለነበረው አርጤክስ ጠጅ አሳላፊ የነበረ አይሁዳዊ (ነህ1፥1-2) ሲሆን አባቱ ኬልቅያስ ይባላል። የኢየሩሳሌምን ፍርስራሽ ሲመለከት ከአርጤክስ ፈቃድ ተቀብሎ የከተማይቱን ሹማምንት ለሥራ በማነሣሳት የጠላቶቹን ተቃውሞ ሳይፈራ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት የበቃ ታላቅ የእምነት ሰው ነው።

(ነህ1፥1-4) ያለውን ገጸ ንባብ በመጥቀስ ጸሐፊው ነህምያ እንደሆነ መናገር የሚቻል ሲሆን የተጻፈበት ዘመን በ446 ዓ.ዓ በኢየሩሳሌም ነው። መጽሐፈ ነህምያ 13 ምዕራፎችን የያዘ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

የኢየሩሳሌም ቅጥር በነህምያ አስተባባሪነት መታነጹን ይናገራል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-2)፡-ነህምያ ወደ ኢየሩሳሌም የሚመለሰው ቅጽሮች በመፈራረሳቸው ምክንያት እንደሆነ ተገልጸል፡፡
2. (ከምዕ 3-6)፡- የኢየሩሳሌምን ቅጽሮችና በሮች መሥራቱን ያወሳል፡፡
3. (ከምዕ 7-13)፡- አምልኮተ እግዚአብሔር መመለሱን ነህምያ የእግዚአብሔር ቤት ማስተዳደሩን

ማስታወሻ፡- መጽሐፈ ዕዝራ እና መጽሐፈ ነህምያ እንደ አንድ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ናቸው፡፡

ጎ. መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል

የቃሉ ትርጉም በግእዙ የጠጣ ማለት ነው፡፡ ይህ ስም የካህኑና የነብዩ የዕዝራ ድርብ ስም ነው፡፡ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ራሱ ዕዝራ ሲሆን 13 ምዕራፎች ሲኖሩት የተጻፈውም በ457ዓ.ዓ በኢየሩሳሌም እንደሆነ ይታመናል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ዕዝራ በባቢሎን ምርኮ ሳለ ስላያቸው ራዕዮች የጥቂዎቹ መልስ እና መንፈሳዊ ጸጋ እና እውቀት ተሰጥቶት ቅዱሳት መጻሕፍትን መጻፉን ይናገራል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-3)፡- ካህኑ ዕዝራ ከመልዓኩ ዑራኤል ጋር መነጋገሩን
2. (ከምዕ 4-7)፡- ስለአእማደ ምስጢራት፣ ስለታጥአንና ጻድቃን ያየው ራዕይ
3. (ከምዕ 8-13)፡- ካህኑ ዕዝራ በጾም በጸሎት ስለተገለጸለት ታላቅ ምስጢር ተጽፏል፡፡

ነ. መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ

የመጽሐፉ ጸሐፊ የተጻፈበት ቦታ እና ጊዜው ከመጀመሪያው መጽሐፍ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ዘጠኝ ምዕራፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

በመጽሐፈ ዜና መዋ ከምዕ 35 እስከ 36፣ ከምዕ 2 እስከ 9 እና በነህ ከምዕ 7-8 ያለውን ታሪክ በስፋት በድጋሚ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-2)፡- እስራኤላውያን ከምርኮ መልስ ቤተ መቅደስ መሥራታቸውን
2. (ከምዕ 3-4)፡- በዳርዮስ ፊት ሦስት ሰዎች ስለመከራከራቸው፡፡
3. (ከምዕ 5-7)፡- ቤተ መቅደስ በዳርዮስ ፈቃድ ስለመሠራቱ
4. (ከምዕ 8-9)፡- ዕዝራ ሕጉን ማንበቡና ኢየሩሳሌም በፋርስ ንጉሥ ስለመወረሯ

ማስታወሻ፡- እንደ ቤተክርስቲያናችን የቅዱሳት መጽሐፍት ቁጥር መሠረት መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል እና መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ እንደ አንድ የሚቆጠሩ መጻሕፍት ናቸው፡፡

ኘ. መጽሐፈ ጦቢት

ጦቢት ማለት መልካም፣ እውነተኛ ቸር ማለት ነው፡፡ መጽሐፉ ከ700-500 ዓ.ዓ ባለው ጊዜ እንደተጻፈ የሚታመን ሲሆን በምርኮ የነበሩ አይሁድ እንደጻፉትም ይነገራል፡፡ መጽሐፈ ጦቢት 14 ምዕራፎች ሲኖረው በነነዌ ተጽፏል የሚልም ግምት አለ፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፈ ጦቢት የጦቢት ቤተሰቦች በመልዓኩ ሩፋኤል አማካኝነት የተደረገለትን እርዳታ እንዲሁም በሃይማኖት ጸንቶ መልካም ሥራን መሥራት ጠቃሚ እንደሆነ የሚናገር ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-3)፡- ጦቢት በበጎ ሥራ እያለ ስለደረሰበት መከራ እና ሣራ ከተባለች ሴት ጋር ጸሎታቸው ስለመሰማቱ፡፡
2. (ከምዕ 4-12)፡- የጦቢት ልጅ መልዓኩ ቅዱስ ሩፋኤል አዛርያስ በተባለ ሰው ተመስሎ እንዴት እንደረዳው፡፡
3. (ከምዕ 13-14)፡- ጦቢት ለእግዚአብሔር ምስጋና ስለማቅረቡ ለልጁ ስለመከረው ምክር እና ስለነነዌ ጥፋት እንዲሁም ከ700-500 ዓ.ዓ ስለ ተፈጸመው ታሪክ እና ስለ ቤተመቅደስ መታነጽ ይናገራል፡፡

አ. መጽሐፈ ዮዲት

የስሟ ትርጉም ኃያል፣ ተጋዳይ፣ አሸናፊ ማለት ነው፡፡ መጽሐፉን ማን እንደጻፈው በትክክል ባይታወቅም በስደት የነበሩ አይሁድ እንደሆኑ ይታመናል፡፡ መጽሐፈ ዮዲት በ600ዓ.ዓ በኢየሩሳሌም የተጻፈ 16 ምዕራፎች ያሉት የታሪክ መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፈ ዮዲት ንጉሥ ናቡከደነፆር እስራኤላውያንን ለመማረክ የላከውን ሆሊፎርኒስ የተባለውን የጦር መሪ ዮዲት የተባለች ሴት ወገኖቿን ከጠላት ለማዳን እንዴት እንደገደለችው የሚተርክ ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-7)፡- የእስራኤላውያን ፍራቻ እና የሆሊፎርኒስ የጦር ዘመቻ
2. (ከምዕ 8-15)፡- ዮዲት እንዴት በጥበብ ወገኖቿን እንዳዳነች
3. (ከምዕ 16)፡- ዮዲት ለእግዚአብሔር ያቀረበችውን ምስጋናና ዕረፍቷን ይተርካል፡፡

ከ. መጽሐፍ አስቴር

በፋርስ ቋንቋ አስቴር ማለት ኮከብ ማለት እንደሆነ ይነገራል፡፡ አንዳንድ ግን አስቴር ‹እሸታር› ከሚባል ከአንዲት የባቢሎን ጣኦት ስም የተገኘ ነው ይላሉ፡፡ የዕብራይስጥ ስሟ ሀዳሳ ነው፡፡ ያሳደጋት የአጎትዋ ልጅ መርዶክዮስ ሲሆን የፋርስ ንጉሥ አርጤክስን ለማግባት በቅታለች፡፡መጽሐፈ አስቴር በአጎትዋ በመርዶክዮስ በፋርስ በባሊሎን የተጻፈ ሲሆን የተጻፈበትም ዘመን ከ586-464 ዓ.ዓ ባለው ጊዜ ነው፡፡ መጽሐፉ 10 ምዕራፎች የያዘ ታሪክ መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

የአይሁድ ጠላት የነበረው ሐማ አይሁድን ሁሉ ለማጥፋት ባሰበ ጊዜ አስቴር ንጉሡን በመለመን እንዳዳነቻቸው የሚተርክ መጽሐፍ ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-2)፡- አርጤክስ ሚስቱ አስጢንን ፈቶ አስቴርን ማግባቱ
2. (ከምዕ 3-5)፡- ሐማ እስራኤል ለማጥፋት እንቅስቃሴ ስለመጀመሩ
3. (ከምዕ 6-10)፡- የሐማ ዕቅድ መክሸፍና አስቴር በጸሎት ወገኖቿን ስለማዳኗ

ማስታወሻ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጽሐፈ አስቴር ስም የሚጠሩ ሁለት መጽሐፍት ሲኖሩ ጸሐፊያቸው መርዶክዮስ ነው፡፡ እነዚህ መጽሐፍት አንዱ በ66ቱ ሌላው በ81ዱ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል፡፡ እነዚህ መጽሐፍት አጠቃላይ ይዞታቸው ቢመሳሰልም አንዳንድ ልዩነት አሏቸው፡፡

መጽሐፈ አስቴር የ66ቱ	*መጽሐፈ አስቴር የ81ዱ*
1. ስመ እግዚአብሔር አልተጠቀሰበትም	1. ስመ እግዚአብሔር ተጠቅሶበታል
2. ስለ መርዶክዮስ ሕልም አይናገርም	2. ስለ መርዶክዮስ ሕልም በመጽሐፉ መጀመሪያ እና ላይ ተጠቅሷል
3. 10 ምዕራፎች አሉት	3. 11 ምዕራፎች አሉት

ኸ. መጽሐፈ መቃብያን

በዓለም ላይ በመቃብያን ስም የሚጠሩ 8 መጽሐፍት አሉ፡፡ በግእዝ መጽሐፍ የታወቁ አራት ሲሆኑ በግሪኩ የታወቁ ደግሞ 4 ናቸው፡፡ በግእዙ ከሚገኙት ውስጥ ቤተክርስቲያን መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ እና ካልዕን ከቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ቆጥራ የምትቀበል ሲሆን መቃብያን ሣልስን ከይዘቱ አንጻር (የብሉይ ኪዳንን ታሪክ እየገለጸ ጽድቅና ኩነኔን እያነጻጸረ ስለሚሰብክ) ከአዋልድ መጻህፍት ጋር መድባ ትቀበለዋለች፡፡ አራተኛውን መጽሐፈ መቃብያን ደግሞ በሌላ ስሙ መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደኮርዮን በመባል ይታወቃል፡፡

1. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በዕብራይስጥ ቋንቋ በ103 ዓ.ዓ ሲሆን 36 ምዕራፎች ሲኖሩት አንድ አይሁዳዊ ፍልስጤም እንደጻፈው ይገመታል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ጺሩዳይን የተባለው አመጸኛ ንጉሥ የመቃቢስ ዘብንያም ልጆች በእውነተኛ ሃይማኖታቸው ምክንያት እንዴት እንዳሰቃያቸው ይተርካል።

አከፋፈሉ፦

1. (ከምዕ 1-5)፦ ስለ ንጉሡ እና ስለ መቃቢስ ልጆች ስቃይና ሰማዕትነት
2. (ከምዕ 6-11)፦ ስለ ዳግም ምጽአት
3. (ከምዕ 12-36)፦ በብሉይ ስለነበሩ አባቶች እና ስለ እስራኤላውያን ይተርካል።

2. መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ

በግሪክ ቋንቋ በ1ኛ መ.ክ.ዘ እንደተጻፈ የሚነገርለት ይህ መጽሐፍ 21 ምዕራፎችን ይዟል።

የመጽሐፉ ይዘት

መቃቢስ የተባለ የሞአብ ንጉሥ እስራኤልን ሊቀጣ ተልኮ ስቃይ እንዳጸናባቸው በአንድ ነቢይ ተመክሮ ንስሐ ገብቶ ከሞተ በኋላ ጺሩዳይን የተባለ ንጉሥ የመቃቢስ ልጆችን እንዴት እንዳሰቃያቸው የሚገልጽ መጽሐፍ ነው።

አከፋፈሉ፦

1. (ከምዕ 1-4)፦ መቃቢስ ዘሞአብ የተባለው ንጉሥ ያደረሰውን ጥፋት በኋላም ንስሐ ገብቶ መልካም ሠርቶ ማረፉን
2. (ከምዕ 5-12)፦ የመቃቢስ ልጆች በሃይማኖታቸው የደረሰባቸውን ስቃይ
3. (ከምዕ 13-21)፦ የመቃቢስን ልጆች መሠረት ተደርጎ ስለትንሣኤ ሙታን ለማያምኑ የተሰጠ መልስ

3. መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ

መጽሐፉ በግሪክ ቋንቋ በ1ኛ መቶ ክ.ዘ የተጻፈ 10 ምዕራፎች ያሉት የታሪክ መጽሐፍ ነው። ጸሐፊው እና ቦታው በውል አይታወቅም።

የመጽሐፉ ይዘት

የብሉይ ኪዳንን ታሪኮች እየጠቀሰ የፅድቅና የኩነኔን የትንሣኤ ሙታንን ነገር የሚያብራራ መጽሐፍ ነው።

አከፋፈሉ፦

1. (ከምዕ 1-3)፦ ስለ አዳምና ሔዋን ውድቀት
2. (ከምዕ 4-6)፦ ስለ ሰይጣን ውድቀት፣ስለ ጌታ ማዳን፣ስለኃጢአት እና ጻድቃን
3. (ከምዕ 7-10)፦ ስለ እግዚአብሔር ስለማመን እና ስለ ኢዮብ ይናገራል።

ወ. መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደኮርዮን

ዮሴፍ ማለት ይጨመር ማለት ነው፡፡ የመጽሐፉ ጸሐፊ የአይሁድ ታሪክ ጸሐፊ የሆነው ዮሴፍ ወልደኮርዮን ነው፡፡ መጽሐፉ በግሪክ ቋንቋ በ1ኛው መቶ ክ.ዘ እንደተጻፈ ይነገራል፡፡ 8 ምዕራፎችም አሉት፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ከአዳም ጀምሮ እስከ 70 ዓ.ም ድረስ ያለውን ታሪክ አካቶ ይተርካል፡፡ ይህም ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ ኢየሩሳሌም በጥጦስ እስከ ጠፋችበት ዘመን ያለው ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. ስለ አዳም
2. ስለ ንጉሥ አንጥያኮስ መቄዶናው ስለ ዮናናውያን ንጉሥ
3. ስለ የእስክንድርያ ንግሥት የህርቃሎስና የአስትሮቦሎስ ልጅ
4. ስለ ህርቃሎስ ከፋርስ መግባትና መገደል
5. ስለ አስቴር ንግሥና ስለ አርክላኦስ ታሪክ
6. ስለ ሄሮድስ ልጅ አርክላሶስ ታሪክ
7. ስለ ስምኦን ያርከሃዊ
8. ስለ ቤተመቅደስ ሮማውያን ከአይሁድ ስለመጠላታቸው ይተርካል፡፡

ማስታወሻ፡- መጽሐፉ በሌላ አጠራር መጽሐፈ ዜና አይሁድ መጽሐፈ ዜና ሥርው እንዲሁም በፍትሐ ነገሥት ተጨማሪ የመቃብያን መጽሐፍ ተብሎ ይጠራል፡፡

ዘ. መጽሐፈ ኩፋሌ

ኩፋሌ ማለት የተከፈለ ማለት ነው፡፡ የተከፈለውም ከኦሪት ነው፡፡ መጽሐፉን የጻፈው ሊቀ ነብያት ሙሴ ሲሆን የተጻፈበትም ዘመን በ1500 ዓ.ዓ በሲና ምድረ በዳ ነው፡፡ መጽሐፈ ኩፋሌ 34 ምዕራፎች የያዘ የታሪክ መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ከሥነ ፍጥረት ጀምሮ እስራኤላውያን ከግብጽ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ይተርካል፡፡ የአርዕስተ አበውንም ዘመን በሱባኤ ይገልጻል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ምዕ 1)፡- ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ስለመነጋገሩ
2. (ከምዕ 2-17)፡- ከአዳም እስከ አብርሃም ድረስ ያለውን ታሪክ
3. (ከምዕ 18-32)፡- የያእቆብና የልጆቹ ታሪክ
4. (ከምዕ 33-34)፡-የሙሴን አነሣስና በግብጻውያን ላይ ያገኘውን ድል ይገልጻል፡፡

ዠ. መጽሐፈ ሄኖክ

ሄኖክ ማለት ተሐድሶ ማለት ነው፡፡ ሄኖክ ከአዳም ጀምሮ ሲቆጠር ሰባተኛ ትውልድ ሲሆን በሕይወት ሥጋ ሳለ እግዚአብሔርን በማስደሰቱ ሞትን ሳይቀምስ ወደ ብሔረ ሕያዋን ያረገ አባት ነው፡፡ በዚያም እያለ የሚሆነውንና የሆነውን እንዲሁም የተለያዩ ምስጢራት ተገልጾለት ጽፎታል፡፡ መጽሐፉ በ4014 ዓ.ዓ.ቅ.ል.ክ የተጻፈ ሲሆን 42 ምዕራፎችን ይዟል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፉ ስለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለቅዱሳን መላዕክት፣ ስለጻድቃን እና ኃጥአን፣ ስለፀሀይና ጨረቃ ስለኖህ ዘመን ስለተፈጸሙ ታሪኮች ይናገራል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-20)፡- ስለቅዱሳን መላእክት፣ ስለደቂቀ ሴት፣ ስለ ኢጋንንት እና ስለ ጌታችን ይናገራል
2. (ከምዕ 21-26)፡- ስለ ፀሀይና ጨረቃ፣ ስለከዋክብት ዑደትና ወቅታት ይናገራል፡፡
3. (ከምዕ 27-35)፡- ስለእስራኤላውያን ከግብጽ መውጣት፣ ስለካህናትና ነቢያት ፣ስለ መሳፍንትና ነገሥታት ይናገራል፡፡
4. (ከምዕ 36-42)፡- ስለ ጻድቃንና ኃጥአን ዋጋና ቦታ ይገልጽልናል፡፡

3 □መዌሙር እና □ዝበብ መጻሕፍት

መዝሙር ማለት ምስጋና ማለት ሲሆን ጥበብ ሲባል ደግሞ ማስተዋል፣ ማገናዘብ፣ ማንኛውም ነገር ለማፅ□ት የመመርመር ችሎታ□ወዘተ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ከላይ በርዕሱ ውስጥ የሚካተቱ መጻሕፍት እግዚአብሔር አምላካችንን ማመስገኛ □ሎታችንን ማቅረቢያ እንዲሁም ስለ ዓበበ እግዚአብሔር በሰፊው ተጽፈው የምናገኝባቸው ናቸው፡፡ በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ በሰምና ወርቅ መል□ □ዙ□ኘ □ሑፎች በመኖራቸው የቅኔ መጻሕፍትም ይባላሉ።

ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ የመዝሙርና የጥበብ መጻሕፍት ተብለ□ ተለጁተ□ □ሚታወቁት ስምንት መጻሕፍት ብቻ ናቸው፡ ፡ከዚህ ቀጥሎ እነርሱን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

ሀ. መጽሐፈ ኢዮብ

ኢዮብ ማለት አበባ፣ ጨረቃ ማለት ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ መቼና በማን እንደተጻፈ በእርግጠኝነት አይታ□ቅም፡፡ ነገር ግን አንዳንዶች ኢዮብ፣ ሙሴ፣ ሰሎሞን፣ ኢሳይያስ፣ ባሮክ ኤልሁም ናቸው ሲሉ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ደግሞ ኤልሁ ነው ይላሉ፡፡

መ□ሐፉ አርባ ሁለት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን በስድ ንባብ መልክ ከተጻፉት የመጀመሪያው እና የመጨረሻው ክፍሎች በስተቀር አብዛኛው ምዕራፎች በግጥም መልክ የተጻፉ ናቸው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

□እግዚአብሔርን በሚወዱና ለሕጉ በማታ□□ ሰዎች ላይ መከራ ሊደርስ □እንደሚችል በትእግስት ካሳለፉት መከራው እንደሚወገድ በረከቱም እጥ አ እንደሚሆንላቸው ያወሳል፡፡

አከኛ□ሉ፡-

1. (ከምክ 1-3)፡- □□ቁ ኢ□ብ በ□ቀ□ □እግዚአብሔር በሰይጣን መፈተኑን
2. (ከምክ 4-37)፡- ኢዮብን ጓደኞቹ የተናገሩት ነገር
3. (ከምክ 38-42)፡- □እግዚአብሔርን ትምህርትና የኢዮብን እጥፍ በረከት ይናገራሉ፡፡

ለ. መዝሙረ ዳዊት

ዳዊት ማለት የተመረጠ፤ ልብ አምላክ ማለት ነው፡፡ ከነገደ ይሁዳ የተመረጠ የእሴይ ልጅ ነው፡፡ እግዚአብሔር አምላክ ዳዊትን ከበግ እረኝነት ወደ ንግሥና፣ ከንግሥና ወደ ነቢይነትና ወደ ሌሎች የክብር ደረጃዎች አምጥቶታል፡፡ ዳዊትን ቀብቶ ያነገሠው ሳሙኤል ሲሆን በነገሠም ጊዜ ሰባት የመንፈስ ቅዱስ ሀብታት ተሰጥተውታል፡፡

መዝሙረ ዳዊትን አሁን ባለበት ሁኔታ ያዘጋቸው ካህኑ ዕዝራ ነው፡፡ መዝሙሮቹ በተለያዩ ዘመናት እንጂ በአንድ ዘመን ብቻ የተዘጋጁ አይደሉም፡፡ መዝሙረ ዳዊት በውስጡ 150 መዝሙርና ጸሎት፤ ትምህርትና ቅኔ ይዟል፡፡ መዝሙረ ዳዊት ብዙውን ጊዜ የዳዊት መዝሙር የሚባልበት ምክንያት አብዛኛውን መዝሙር □እርሱ ስለደረሳቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን ከ150ው መዝሙሮች ውስጥ በሌሎች ሰዎች የተደረሱ □እንዳሉ ከመዝሙሩ ከራሱ መገንዘብ ይችላል፡፡ መዝሙረ ዳዊት ለቤተ ክርስቲያናችን የጸሎት፣ የመዝሙር መጻሕፍት መሠረት ወይም ምንጭ ነው፡፡ መዝሙረ ዳዊት መዘምራን በዜማ፣ መነኮሳትና ካህናት ቀንና ሌሊት እግዚአብሔር አምላክን የሚያመሰግኑበት፣ ምእመናን ዘወትር እየጸለዩበት ኢጋንንትን የሚያርቁበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፡፡

መዜሙረ ዳዊት የተጻፈው በ1000 ቅ.ል ክርስቶስ ሲሆን የተጻፈበትም ቦታ በኢየሩሳሌም ነው

የመጽሐፉ ይዘት

መዝሙረ ዳዊት የሰውን የህይወት ዘመን ሳይለይ ሰው በሕይወቱ የሚያጋጥሙትን ሀዘንና ደስታ□ ፣ መልካምና ክፋ፣ መውደቅና መነሣት፣ ችግርና ምቾት ወዘተ… የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

አከፋ□ል፡-መዝሙረ ዳዊት በአምስት ክፍሎች የተከፈለ መጽሐፍ ነው፡፡

1. ከመዜ 1 እስከ መዜ 40
2. ከመዜ 41 እስከ መዜ 71
3. ከመዜ 71 እስከ መዜ 88
4. ከመዜ 89 እስከ መዜ 105
5. ከመዜ 106 እስከ መዜ 150 ናቸው፡፡

እያንዳንዱ ክፍል ፍጻሜ ላይ “ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም እግዚአብሔር ይባረክ አሜን አሜን” የሚሉ ቃላት ይገኙባቸዋል፡፡ በቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት አሥሩን መዝሙሮች በአንድነት “አንድ ንኡሥ” የሚል ስያሜ እየሰጡ በአሥራ አምስት ይከፍሉታል፡፡

ሐ. መጽሐ□ ምሣሌ

መጽሐፈ ምሳሌን የጻፈው መፍቀሬ ዓበብ ሰሎሞን ነው። መጽሐፉ የተጻፈው በግጥም መልክ ነው። ምክንያቱም በግጥም የተሰጠ ትምህርት በልብ ይኖራልና። መጽሐፉ 24 ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የተጻፈበትም ዘመን በ950 ቅ.ል. ክርስቶስ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

መ□ሐኛ □እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዴት መኖር □እንዳለበት ያስተምራል። በአጠቃላይ መጽሐፉ ትምህርትን ምክርን በምሳሌ የሚያስተምር ነው።

አከኛ□ሉ፡-

1. (ከምዕ 1-9)፡- ስለ ዓበብ ቸለነ፤ ጥበብን የመማር ጥቅምና የአለመማርን ጉዳት ያወሳል
2. (ከምዕ 1ው22)፡- በሥነ ምግባር ለመታነጽ የሚረዱ ትምህርቶችን በተለያዩ ምሳሌዎች ጽ□ል□ል
3. (ከምዕ 23-24)፡- በቀላል የስብከት መንገድ ጥበብን ለመማር ትእዛዞች፣ ምክሮችና መመሪያዎች ተጽፈዋል።

መ. መ□ሐ□ ተፅሳ□

መጽሐፈ ተግሳጽ በአቀራረቡ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት አለው። ተግሳጽ ማለት ምክር □እንደማለት ነው።

መ□ሐፉ ከንጉሥ ሰሎሞን፣ አጉርና በሙኤል የተጻፈ ነው። በመጽሐፉ ያሉት ምሳሌዎች በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ ዘመን በነበሩ ነቢያት የተሰበሰቡ ናቸው። መጽሐፈ ተግሳጽ 7 ምዕራፍ ያሉት መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ እንደሌሎች የሰለሞን መጽሐፍ በኢየሩሳሌም በ7ወመ □□ ተ□ጠል።

የመጽሐፉ ይዘት

መንፈሳዊ ምክርን የያዘ □እግዚአብሔርን ስለመፍራት የሚያስተምር መጽሐፍ ነው።

አከኛ□ሉ፡-

1. (ከምዕ 1-5)፡- የይሁዳ ንጉሥ የሕዝቅያስ ሰዎች የቀዱአቸውን የሰለሞን ምሳሌዎችን ጽ□ል
2. (ምክ 6)፡- የማሣ አገር ሰው የያቂ ልጅ አጉር ለኢቲኤልና ለኡካል የተናገረው ቃል ተ□ጠል
3. (ምክ 7)፡- የማሣ ንጉሥ ልሙኤል የተናገረውን ትምህርት ይዟል።

ማስታ□ሻ ፡- መጽሐፈ ተግሳጽ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱን ችሎ □እንደ አንድ መጽሐአ የተቀመጠ ሳይሆን ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር በአንድነት ከምዕራፍ 25 ጀምሮ እስከ 31 ድረስ በመካተት ነው። በግእዙ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ራሱን ችሎ ሰባት ምዕራፎች የያዘ መጽሐፍ ነው።

ሠ. መ□ሐ□ መ□ብብ

መክብብ ማለት ሰባኪ፣ አስተማሪ ማለት ነው። መጽሐፉ ይህን ዓይነት ስያሜ ያገኘበት ምክንያት «ሰባኪው □እንዲህ ይላል» በማለት የተለያየ ስብከትና ትምህርቶች ስለሚያቀርብ ነው።

ይህን መጽሐፍ የጻፈው ጠቢቡ ሰሎሞን ሲሆን 12 ምዕራፎችንም አካቷል። በመጽሐፉ ውስጥ 37 ጊዜ «ከንቱ» የሚለውን ቃል □እናገኛለን።

የመጽሐፉ ይዘት፡-መጽሐፉ ተቃራኒ ነገሮችን □እያነሣ ሁሉም ከንቱ መሆናቸውን የሚዘግብ ነው።

አከፋ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- ከፀሐይ በታች በዓለም ላይ ሁሉም ዙሮ ዙሮ እንደሚመጣ ፍጻሜም □እንደሌለው ጽ□ል□ል።
2. (ምክ 2)፡- በ□ህ □ሉል □□ለም □ስታ የተባለውን ሁሉ ከንቱና ነፋስን □እንደመከተል □እንደሆነ ይተርከል።
3. (ከምዕ 3-11)፡- □እግዚአብሔር በነገሩ ሁሉ ከሌለ ሁሉ ከንቱ ነው ይላል።
4. (ምክ 12)፡- በዚህ ክፍል አጥጋቢ ደስታና የተትረፈረፈ ሕይወት በዓለም ነገር በማናቸውም በኩል□እንደማይገኝ ተገልጿል።

ረ. መኃል□ መኃል□ ዘሰሎሞን

የቃሉ ትርጉም ከመዝሙራት ሁሉ የሚበልጥ የሰሎሞን መዝሙር ማለት ነው። ይህ መጽሐፍ በጠቢቡ ሰለሞን የተጻፈ 8 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

በሁለት ፍቅረኛሞች መካከል የሚደረግ ንግግር ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም ሲባል ስለ

እግዚአብሔርና ስለ እስራኤል፣ ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር በባልና በሚስት □□መሰለ የሚናገር ነው። መጽሐፉ ስለእመቤታችንና ስለ ምስጢረ ቁርባንም ጸ□ሳል።

አከፋ□ሉ፡- ይህ መጽሐፍ በአራት ዐበይት ክፍሎች ይከፈላል

- ሙሽሪት ለሙሽራው በቅርብ የምታደርገው ንግግር
- ሙሽሪት ለሙሽራው በሩቅ □ምታደርገው ንግግር
- ሙሽራው ለሙሽሪት በቅርብ የሚያደርገው ንግግር
- በሙሽራውና በሙሽሪት መካከል ያለው ጥያቄና መልስ ተጽፏል።

❖ ይህን መጽሐፍ ሦስት ዓይነት ሰዎች በመቀባበል ተናግረውታል

ሀ. ሙሽራው፡- 11 ጊዜ

ለ. ሙሽራይቱ፡- 17 ጊዜ

ሐ. የኢየሩሳሌም ቆነጃጅት 4 ጊዜ

ሰ. መጽሐፈ ጥበብ

ጥበብ በቁሙ ሲፈታ እውቀት፣ ብልሃት፣ ፈሊጥ፣ ሕከምና፣ ምክር ማለት ነው። መጽሐፈ ጥበብ 19 ምዕራፎች ያሉት በጠቢቡ ሰሎሞን የተጻፈ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በአቀራረቡ ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት አለው። መጽሐፈ ጥበብ በ900 ዓ.ዓ አካባቢ በኢየሩሳሌም ከተማ ተጽፏል።

የመጽሐፉ ይዘት

የመጽሐፉ አጠቃላይ ይዘት ስለ ጥበብ በማውሳት ሰው ጥበብን እንዲፈልግ ይመክራል።

አከፋ□ፈ፡- መጽሐፈ ጥበብ በ19 ምዕራፎች እና በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል

1. **(ከምዕ 1- 6)**፡- ስለ ነገሥታትና ስለ ክርስቶስ
2. **(ከምዕ 7-15)**፡- ስለ ሰው ተፈጥሮና ጣኦት አምልኮ
3. **(ከምዕ 16-19)**፡- ስለ ግብፃውያን እና ስለ ኢየሩሳሌም ይናገራል።

ረ. መጽሐፈ ሲራክ

ሲራክ ማለት ጸሐፊ ማለት ነው። የመጽሐፈ ሲራክ ጸሐፊው ኢያሱ ወልደ አልዓዛር ወልደ ሲራክ ይባላል። መጽሐፉ 51 ምእራፎች ሲኖሩት በአቀራረቡ ከሰሎሞን መጽሐፈ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይነት አለው። መጽሐፉ ከጌታ ልደት 180 ዓመት በፊት ጸሐፊው እግዚአብሔርን መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥበብ ለምኖ ተገልጾለት የጻፈው ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፈ ሲራክ ከአዳም ጀምሮ ያሉትን አበው ታሪክ ይገልጻል። ለመንፈሳዊ እና ለሥጋዊ የሚሆን ምክርና ጥበብን ይገልጻል።

አከፋ□ፈ፡- መጽሐፈ ሲራክ 51 ምዕራፎች ሲኖሩት በ5 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. **(ከምዕ 1-10)**፡- ስለ ጥበብና ፈሪሃ እግዚአብሔር፣ ቤተሰባዊ ኑሮ፣ ስለ ዝምታና ትእግስት ይገልጻል።
2. **(ከምዕ 11-20)**፡- ስለ ፍርድ፣ ስለ ምጽዋትና ስለ ሥነ ፍጥረት ይናገራል።
3. **(ከምዕ 21-30)**፡- ስለ ንስሐ፣ ስለ ንጽሕና፣ ስለ ብልሕ ሰውና ስለ 5ቱ አዕማደ ምስጢር
4. **(ከምዕ 31-41)**፡- ስለመባዕ፣ ስለገንዘብ፣ ስለምክር፣ ስለምግባርና ሃይማኖት
5. **(ከምዕ 42-51)**፡- ስለ ኃጢአተኞች፣ ስለ ሥነ ፍጥረት፣ ስለ ቀደምት አበውና ነገሥታት፣ መሳፍንት፣ ነብያትና ካህናት ይናገራል።

4 የትንቢት ክፍል መጻሕፍት

ነብይ ማለት አፈ አምላክ / የእግዚአብሔር አፍ / ወይም መምህር፣ ሰባኪ ማለት ነው። ስሙም የሚሰጠው ትንቢት የመናገር፣ራዕይ የማየት ጸጋ ለተሰጣቸው እውነተኛ ነቢያት ነው።

የነቢያት አከፋፈል

ነብያት ዐበይትና ደቂቅ፣የቃልና የጽሑፍ፣□እውነተኛና ሐሰተኛ፣ ወንዶችና ሴቶች በመባል ሊከፈሉ ይችላሉ።

- ዐበይት ነብያት፡- ዐበይት ማለት ታላላቅ ማለት ነው፡፡ ዐበይት ነብያት የተባሉበትም ምክንያት የጻፏቸውም መጽሐፍት በምዕራአ ብ□ ስለሆኑ በእትሜያቸውና ከያዟቸው ምስጢራት ወይም ታሪክ አንፃር ነው፡፡ ዐበይት ነብያት የሚባሉት በቁጥር አራት ናቸው እነርሱም ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ ሕዝቅኤልና ዳንኤል ናቸው፡፡

- ደቂቅ ነብያት፡- ደቂቅ ማለት ትንንሽ ማለት ነው፡፡ ደቂቅ ነብያት የተባሉበትም ምክንያት የጻፏቸው መጽሐፍ በምዕራፍ ትንሽ በመሆኑ ከያዟቸው ታሪክና ትንቢት አንጻር ነው፡፡ ደቂቅ ነብያት በቁጥር 12 ናቸው፡፡ እነርሱም ሆሴዕ፣ አሞጽ፣ ሚክያስ፣ ኢዩኤል፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም፣ ሶፎንያስ፣ ሐጌ፣ ዘካርያስና፣ ሚልክያስ ናቸው፡፡

- የቃል ነብያት፡- ትንቢት ይናገራሉ ግን የተናገሩት ትንቢት በመጽሐፍ ያልሰፈረላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጋድ፣ ኤልያስ፣ ኤልሳዕ፣ ናታን የመሳሰሉት

- □□ሑፍ ነብያት፡- የተናገሩት ትንቢት በመጽሐፍ ሰፍሮ የምናገኝላቸው ነብያት ናቸው፡፡ ለምሳሌ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ ሆሴዕ ወዘተ…

- እውነተኛ ነብያት፡- እግዚአብሔር መርጧቸውና ልኳቸው ሕዝቡን ከሚመጣው ቁጣ □እንዲጠበቁ የሚሰብኩና የሚያስተምሩ እግዚአብሔር በራዕይ ተገልጦላቸው እውነተኛውን ነገር ለሕዝቡ የሚያደርሱ ናቸው፡፡

- ሐሰተኛ ነብያት፡-□እግዚአብሔር ሳይመርጣቸውና ሳይልካቸው ተጠርተናል ተመርጠናል በራዕይ ተገልጸልናል በማለት ሕዝቡን የሚያውኩ ናቸው፡፡ ከሐዲስ ኪዳን ፀራዊ ቢጽ ሐሳውያን፣ መናፍቃን ይባላሉ፡፡ (ማቴ 7÷15) (2ኛ ጢሞ 3÷13)፡፡

    - ❖ ሐሰተኛ መሆናቸው በምን ይታ□ቃል ቢሉ፡-
        - የተናገሩት ሳይፈጸም ሲቀር (□□ 18÷20)
        - ባዕድ አምልኮ ሲከተሉ (ዘዳ 13÷1-14)
        - አካሄዳቸው ክፉ ሲሆን (ኤር 23÷16)
        - ጎጢአት ሲበዛ ንስሐ ሳይሆን ሰላምን ሲሰብኩ (ኤር 6÷14) □□ዙ…

- ሴት ነብያት፡- እነዚህ በጸታቸው ሴት ሆነው ራዕይ የሚያዩ ትንቢት የሚናገሩ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- □ሙሴ እህት ማርያም (ዘጸ 15÷2)፣ □ቦራ (መሳ 4÷14)፣ ሕልዳና (2ኛ ነገ 22÷15)፣ ሃና (ሉቃ 2÷36) □□ዙ ጁዲኖሉ፡፡

እነዚህ ከላይ ያየናቸው ቅዱሳን ነቢያት መጽሐፍቶቻቸውን ከጻፉበት ዘመን አንጻር በሦስት መክፈል እንችላለን፡፡

1· ከምርኮ በፊት የተጻፈ

- እነዚህ በቁጥር አስራ አንድ ናቸው፡፡ እነርሱም ሆሴዕ፣ አሞጽ፣ ሚክያስ፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ አብድዩ፣ ዮናስ፣ ሶፎንያስ፣ ናሆም፣ ዕንባቆም እና ኢዩኤል ናቸው፡፡

2· በምርኮ ቂ□ □ዙ□ኛ

- **በቁጥር 2 ናቸው። ትንቢተ ሕዝቅኤልና ትንቢት ዳንኤል**

3· ከምርኮ በኋላ የተጻፉ

- **ከምርኮ በኋላ የተጻፉ የትንቢት መጽሐፍት ሦስት ናቸው። እነርሱም ሐጌ፣ ዘካርያስና ሚልክያስ ናቸው።**

በአጠቃላይ በዚህ በትንቢት ክፍል መጽሐፍት ውስጥ አስራ ስድስት መጽሐፍትን□እናገኛለን። ቀጥሎ □እያንዳንዱን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፦

ሀ. ትንቢተ ኢሳይአስ

የስሙ ትርጓሜ መድኅኒት ማለት ነው።እናትና አባቱ ደጋግ ሰዎችን ጠይቀው በትምህርቱ በትንቢቱ እንዲረባ እንዲጠቅም ይህን ስም ሰጥተውታል። በሌላ በኩልም ኢሳይያስ ማለት ቅቡዕ እምቅብዓ ትንቢት ማለት ነው። ለነቢይነት□እግዚአብሔር ቀብቶታልን። አባቱ አሞጽ ይባላል ሆኖም ከነቢዩ አሞጽ ሌላ ነው።

የነበረበት ዘመንም በይሁዳ ነገሥታት በዖዝያን፣ በኢዮአታም፣ በአካዝና በአካዝያስ ዘመን ነበር። በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመነ መንግሥት የቤተ መንግሥት አማከሪ ሆኖ ይሠራ ነበር። ነቢይ □እንዲሆን □ተመረጧ□· ዖዝያን ንጉሥ ሆኖ ተሹሞ በነበረበት ዓመት ነው።

ንጉሡ በሞተ በዓመቱ ፅሩም ምስጢር ተገልጦለት ነበር። (ኢሳ 6÷1-2)። ነቢዩ ኢሳይያስ ባለትዳር የነበረ ነቢይ ሲሆን ሚስቱም እንደርሱ ነቢይት ነበረች፤ሁለት ልጆችም ነበራቸው።

ነቢዩ ኢሳይያስ የኖረው እስከ ንጉሥ ምናሴ ዘመን ድረስ ሲሆን ንጉሡ ምናሴ ገና በንስሐ ወደ አምላኩ ከመመለሱ በፊት ኢሳይያስን በመጋዝ አስቆርጦ እንዳስገደለው ይተረካል። /ዕብ 11÷37/

ኢሳይአስ ታላቅ ምሁረ አሪት ነበር። ትንቢቱንም የተናገረው በኢየሩሳሌም ሆኖ ነው። ኢሳይአስ የመጀመሪያው ነቢይ ሳይሆን ከታላላቆች ነቢያት አንዱና የትንቢት መጽሐፉም የመጀመሪያውን □ረጅ የያዘ ነው። መጽሐፉም የተጻፈው ቅ·ል·ክ 700 ዓመት ላይ ሲሆን የተጻፈውም በራሱ በኢሳይያስ ነው። ትንቢተ ኢሳይያስ 66 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

- **በአንድ አምላክ እምነት መጽናት**
- **በእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት መመራት**
- **ስለሚመጣው አዳኝ ንጉሥ /መሲሕ/**
- **ለዘመኑ ነገሥታት ያስተማረው ምክርና የሠጠው ማስጠንቀቂያ**

አከኛ□ሉ፦

1. **(ከምዕ 1-23)፦ ስለ ባቢሎን ምርኮ**

2. (ከምዕ 24-35)፡- ከምርኮ ስለመመለሳቸው
3. (ከምዕ 36-66)፡- ስለ ጽዮን በተለያየ መልኩ ትንቢት ይናገራል።

ለ. ትንቢተ ኤርምያስ

ኤርምያስ ማለት እግዚአብሔር ከፍ ያደርጋል ማለት ሲሆን አባቱ ኬልቅያስ እናቱ ማርታ ጁባላሉ። ሀቱ ጁሁ□ ል□ ስሙ ዓናቶት ይባላል። ኤርምያስ የነበረበት ዘመን ቅ.ል.□ በ7ተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ሲሆን ለነብይነት የተጠራ□ በ15ተኛው ይሁዳ ንጉሥ በኢዩስዮስ ዘመን ነው። ኤርምያስ ልዩ በሆነ ምርጫ ከእናቱ ማኅጸን ጀምሮ የተለየ ነው። (ኤር1÷5-1ወ)

ትንቢተ ኤርምያስን ራሱ ኤርሚያስ በኢየሩሳሌም ሳለ እንደተባፈው የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ። መ□ሐፉ 52 ምዕራፎች አሉት።

የመጽሐፉ ይዘት

እግዚአብሔር ታላቅና ቅዱስ ስለሆነ ሕዝቡ ከክፋት ተመልሰው በፍጹም ልብ ያለሐሰት □ርሱን እንዲያመልኩት ማሳሰብ ነው።

አከፍ□ሉ፡-

1. (ከምዕ 1-21)፡- በኢዩአስ ጊዜ የኤርምያስ የመጀመሪያው መልዕክት
2. (ከምዕ 22-36)፡- በኢዮአክስና በኢዩአቂም ጊዜ በኤርምያስ ላይ ስለተፈጸመ ፍርድና ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን ስለመክበቡ
3. (ከምዕ 37-39)፡- በኢኮንያን፣ በሴዴቅያስ፣ በጎዶልያስ ዘመን ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋትና ስለ ምስታ.ረ ሥፋዳ ተ□ጠል
4. (ከምዕ 4ወ51)፡- በዘመነ ጎዶልያስ ቤተ መቅደስ መፍረሱን ይናገራል።

ሐ. ሰቆቃወ ኤርምያስ

ሰቆቃው ማለት ሙሾ ልቅሶ ማለት ነው። ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይህን መጽሐፍ ኤርምያስ □እንደጻፈው ይናገራሉ። መጽሐፉ 5 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

መ□ሐፉ ኢየሩሳሌም በጠላት እጅ አወዳደቋን የአጥሮቿና የቤተ መቅደስዋ መፍረስን፣ የንብረቷና የሕዝቧን መማረክን መነሻ በማድረግ ነቢዩ ያቀረበውን ሰቆቃ /የሐዘን□እንጉርጉሮ/ ይናገራል።

አከፍ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- ስለ ኢየሩሳሌም መጥፋት
2. (ምክ 2)፡- በኢየሩሳሌም ስለወረደው ቅጣት
3. (ምክ 3)፡- የሕዝቡን ንስሐና በጌታችን ምሕረት መታመናቸው
4. (ምክ 4)፡- ያለፈውን በማስተዋል የሆነ አስፈሪ ድርጊት

5. (ምክ 5)፡- ቄታችን ምሕረቱን እንደመለሰላቸው ይገልጻል።

መ. ተረፈ ኤርምያስ

ተረፈ ማለት የተረፈ፣ የቀረ ማለት ነው። ተረፈ ኤርምያስ ከሰቆቃው ኤርምያስ ቀጥሎ ምዕራፍ 6 ብሎ □ሚጸምር ባለ ስድስት ምዕራፍ መጽሐፍ ነው። ጸሐፊው ባሮክ ነው። (ተረ.ኤር 11÷63)

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፉ ስለ ባቢሎን ምርኮና የምርኮውን ዘመን □እግዚአብሔር ለባሮክና ለአቤሜሌክ □እንዴት አድርጎ □እንዳሳለፈላቸው □እንዲሁም ስለ ኤርምያስ ሰማዕትነት ይናገራል።

አከፍ□ሉ፡-

1. (ምክ 6)፡- ስለ ባቢሎን ጣኦቶች ነቢዩ የተናገረውን ነገር
2. (ከምክ 7-8)፡- ስለ ኢየሩሳሌም ጥፋት ኤርምያስና ባልንጀሮቹ ማልቀሳቸውንና ምድር ንዋያተ ቅድሳትን በአደራ መልክ ስለመቀበሏ
3. (ከምዕ 9-10)፡- የአቤሜሌክና ባሮክ መገናኘትና ወደ ባቢሎን ደብዳቤ መላክቸውን
4. (ምዕ 11)፡- ኤርምያስ ለሕዝቡ ስለ ክርስቶስ ትንቢት ተናግሮ በሰማዕትነት ማረፉን ጽ□ል□ል።

ሠ. መ□ሐ□ ባሮ□

ባሮክ ማለት ቡሩክ ማለት ነው። የነቢዩ ኤርምያስ ታማኝ ወዳጅና ጸሐፊም ነበር። ኤርምያስ በንጉሥ ሴዴቅያስ ዘመን በታሰረ ጊዜ የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ ኤርምያስን ይረዳው ነበር (ኤር 32÷12-16) ነቢዩ ኤርምያስ ከጥቂት አይሁዶች ጋር ወደ ግብጽ እንዲጓዝ በተሰደደ ጊዜም አብሮ ሄዷል። (ኤር 43÷1-7)

መጽሐፈ ባሮክ የተጻፈው በራሱ በባሮክ ሲሆን መጽሐፉንም በባቢሎን በምርኮ በነበረበት ጊዜ ለኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ጽፎ ልኮላቸዋል። መጽሐፉ 5 ምዕራፎችን ይዟል። የተጻፈውም በ586 ዓ.□ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

በምርኮ ስላሉት የአይሁድ ኑሮ ስለ ንስሐ ጸሎትና ለአይሁድ የቀረቡ ምክሮች ይገኙበታል።

አከፍ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡-እስራኤል የእፅዚአብሔርን ሕግ በመርሳታቸው ስደት □እንደሚመጣባቸውና □እንዲጸጸቱ የመከረው ምክር
2. (ምክ 2)፡- ባሮክ ስለበደላቸው የጸለየው ጸሎት
3. (ምክ 3)፡- ሕጉን ቢጠብቁ መልካም ይሆንላቸው እንደነበርና ስለ ጥበብ

4. (ከምዕ 4-5)፡- እስራኤል እግዚአብሔር በቸርነቱ እንደሚመልሳቸውና በክብር □እንደሚኖሩ ጹፏል□ል፡፡

ማስታ□ሻ፡- ሰቆቃው ኤርምያስ፣ ተረፈ ኤርምያስ እና መጽሐፈ ባሮክ በተጻፈበት ጊዜ □መ□ሕአቱ ይዘት ተመሳሳይነት ምክንያት ከትንቢት ኤርምያስ ጋር በመደመር□እንደ አንድ መጽሐፍ ጹቆታራሉ፡፡

ረ. ትንቢተ ሕዝቅኤል

በዕብራይስጥ ቋንቋ አጠራር ይሕዝቅኤል ይባላል ትርጓሜውም ያጸንእ እግዚአብሔር ማለት ሲሆን ወደ አማርኛ ስንመልሰው እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣል ማለት ነው፡፡ የስሙ ትርጉምም ከመጽሐፉ የተወሰደ ነው፡፡ (ሕዝ 3÷14) (ሕዌ 3ው25፤34÷16)፡፡ ሕዝቅኤል በ622 ቅ.ል.□ ተ□ለ□፡፡ ነገዱ ከቤተ ሌዊ ሲሆን ትውልዱ ከቤተ ሳዶቅ ነው፡፡ አባቱ ቡዝ ይባላል፡፡ ከልጅነቱ ጀምሮ የኤርምያስ ደቀመዝሙር እንደነበር ይነገራል፡፡ ሕዝቅኤል ኢኮንያን በተማረከ ጊዜ አብሮ ተማርኳል (ሕዌ 1÷1) ይኖርበት የነበረ ቦታም በኮበር ወንዝ አጠገብ ነበር፡፡ (ሕዝ 3÷15)

ትንቢተ ሕዝቅኤል የተጻፈው በ600ዓ.ዓ ቅድመ ልደተ ክርስቶስ ሲሆን በባቢሎን ምርኮ ጊዜ እንደተጻፈ ይነገራል፡፡ ትንቢተ ሕዝቅኤል 48 ምዕራፎች አሉት፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ ኢየሩሳሌም ውድቀትና መነሣት እንዲሁም ስለ ጌታችንና እመቤታችን ስለ አምስቱ አዕማደ ምስጢርም ይተርክል፡፡

አከፍ□ሉ፡-

1. (ከምዕ 1-24)፡- ከኢየሩሳሌም መውደቅ በፊት የተነገሩ ትንቢቶች
2. (ከምዕ 25-32)፡- በውጭ ሕዝቦች ላይ የተነገሩ ትንቢቶችን ይዟል
3. (ከምዕ 33-39)፡- ናቡከደነጾር ኢየሩሳሌምን ከወረረ በኋላ የተነገሩ ተስፋ ሚጠትን (መመለስን) የሚያበስሩ ትንቢቶች ይገኙበታል
4. (ከምዕ 40ው48)፡- ስለ አዲሱ ሥርዓተ ጽዮን ተጽፏል፡፡

ሰ. ትንቢተ ዳንኤል

ዳንኤል ማለት እግዚአብሔር□እውነተኛ □ኛ /ፈራጅ/ ነው ማለት ነው፡፡ በዕብራይስጥ አነጋገር ዳንኤል ማለት አምላክ ዳኛዬ ነው ፈራጂ ነው ማለት እንደሆነ የቋንቋው ሊቃውንት ይናገራሉ፡፡ ዳንኤል አባቱ ኢዩአቄም እናቱም ሚልያ ይባላሉ፡፡ ነገዱም ከነገደ ይሁዳ ሲሆን ከንጉሣዊ ቤተሰብ በዘመነ ኢዮስያስ ተወለደ /ዳን1÷3-4/

ዳንኤል በቀዳማዊ ፍልሰት እስራኤላዊያን በኤያቄም ዘመን ወደ ባቢሎን 2ቱ ነገድ /የይሁዳና □በንያም/ ሲማረኩ አብሮ ተማርኳል፡፡ ዳንኤል መልካም ጥበበኛና አስተዋይ መፈክረ ሕልም

/□ሕልም ተርጓሚ/ የአስተዳደርም ሰው ነበር (ዳን 4÷1-9፤1ው1-3) ዳንኤል የጾምና የጸሎት ሰው ነው፡፡ □ፀፅ □ዙ□□□ እንደነበር ከመጽሐፉ እንረዳለን (ዳን 6÷10) (ዳን 10÷11)

ይህን መጽሐፍ የጻፈው ራሱ ዳንኤል ሲሆን በባቢሎን□እንደሆነ ሊቀውንቱ ይስማማሉ፡፡ ትንቢተ ዳንኤል 6 ታሪኮችን 4 ራዕዮችን በማካተት 12 ምዕራፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት፡- በስደትና በመከራ ጊዜ በሃይማኖት መጽናት እንደሚገባ፣ ታማኝ ስለሆኑት ስለ ሠለስቱ ደቂቅ፣ ነብዩ የንጉሡን ሕልም ስለ መአታቱ፣ ስለመላእክት፣ ስለክርስቶስ ሰው መሆን፣ ስለ ትንሣኤ ጽተርካል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምክ 1-6)፡- ስድስት ዐበይት ተረኮችን ይዟል
2. (ከምክ 7-12)፡- አራት ራዕዮችን ይዟል

ሸ. መጽሐፈ ሶስና

ሶስና ማለት የዋኒ ርግብ ማለት ነው፡፡ የተጻፈበት ቦታም እንደ ትንቢተ ዳንኤል ነው፡፡ መጽሐፈ ሶስና አንድ ምዕራፍ ያለው በነቢዩ ዳንኤል የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡ ሶስና ከእነ ዳንኤል ጋር በፋርስ በሰደት ትኖር የነበረች ሴት ናት፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

እግዚአብሔርን የምትፈራ ሶስና የተባለች□እስራኤላዊት በዝሙት ወንጀል በሐሰት ተከሳ በድንጋይ ልትወገር ስትል ነቢዩ ዳንኤል ጥበብ በሞላበት ዘዴ እንዴት እንዳዳናት ይተርክል፡፡

አከኛ□ሉ፡-

1. (ከቁ 1-14)፡- የሶስና አስተዳደግ እና የሁለቱ ረበናት ተንኮል
2. (ከቁ 14-43)፡- መምህራኑ ሶስናን በሐሰት መክሰሳቸውና ሶስና ወደ አምላኳ ያቀረበችው ጸሎትን ይዟል
3. (ከቁ 44-66)፡- ነቢዩ ዳንኤል በጥበብ እንዴት ከክስ እንዳዳናትና የመምህራኑ መቀጣትን ይናገራል፡፡

ቀ. □ሎተ ሠለስቱ □ቂቅ

ጸሎት ሠለስቱ ደቂቅ ማለት የሦስቱ ልጆች ጸሎት /መዝሙር/ ማለት ነው፡፡ ሦስቱ ልጆች የተባሉትም ሲትራቅ፣ ሚሳቅ እና አብድናጎ /አናንያ አዛርያ እና ሚሳኤል/ ናቸው፡፡ መጽሐፉ በነብ□ ዳንኤል የተጻፈና አንድ ምዕራፍ ያለው ሲሆን የተጻፈበትም ዘመንና ቦታም እንደ ትንቢተ ዳንኤል ያለ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ከነቢዩ ዳንኤል ጋር በስደት ወደ ባቢሎን ተሰደው የነበሩት ሦስቱ ልጆች ወደሚነድ እቶንእሳት በተጣሉ ጊዜ ለአምላካቸው ያቀረቡት የምስጋና ጸሎትን ይገልጻል (ዳን 3÷1-3ወ)

አከፋፈሉ፡-

1. (ከቁ 1-25)፡- የአናንያ ጸሎትና መልአኩ እሳቱን ማብረዱን
2. (ከቁ 26-66)፡- ሦስቱም በንብረት የዘመሩትን ዝማሬ ይገልጻል

በ. ተረፈ ዳንኤል

ተረፈ ማለት ቀረ፣ የቀረ፣ የተረፈ ማለት ነው። ተረፈ ዳንኤል በነብዩ ዳንኤል የተጻፈ ባለ አንድ ምዕራፍ መጽሐፍ ሲሆን የተጻፈበት ቦታና ዘመንም ከትንቢተ ዳንኤል ጋር ይመሳሰላል። መጽሐፉም (በዳን 6÷4-24) ላይ ከምናገኘው ታሪክ ጋር ተመሳሳይነት ያለውና ታሪኩም በስፋት የተተነተነበት ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

ነቢዩ ፈሪሳዊያንና የባቢሎን ሰዎች ያመልኳቸው የነበሩትን ጣኦታት እንዴት እንዳጠፋና እግዚአብሔር እንዴት ዳንኤልን ከአንበሶች አፍ እንዳዳነው ይናገራል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ከቁ 1-28)፡- ነቢዩ ጣኦታቱን እንዳጠፋ
2. (ከቁ 29-42)፡- ነቢዩ ወደ አንበሶች ጉድጓድ እንዴት እንደተጣለና እግዚአብሔር የሰራለትን ድንቅ ሥራ ይናገራል።

ተ. ትንቢተ ሆሴዕ

ሆሴዕ ማለት እግዚአብሔር ያድናል ማለት ነው። ነቢዩ ሆሴዕ ዳግማዊ ኢዮርብዓም በሰማርያ ነግሦ በነበረበት ዘመን በሰሜናዊ የእስራኤል መንግሥት ተነሥቶ የነበረ ነቢይ ነው። ዘመኑም ክክርስቶስ ልደት በፊት 721 ዓ.ዓ ነው።

ሆሴዕ ትንቢት የተናገረበት ዘመን ዖዝያን፣ ኢዮአታም፣ አካዝና፣ ሕዝቅያስ የሚባሉ የይሁዳ ነገሥታት ነበሩ። በዚህ ዘመንም ነቢዩ አሞጽ ነቢዩ ኢሳይያስና ነቢዩ ሚክያስ ትንቢት ይናገሩ ነበር። ትንቢተ ሆሴዕ 14 ምዕራፍ ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

እግዚአብሔር የማይለወጥ አምላክ ስለሆነ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ በመመለስ እንዲድኑ ጥሪ ማስተላለፍ ነው።

አከፋፈሉ፡- ትንቢተ ሆሴዕ 14 ምዕራፎች ሲኖሩት በ2 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. (ከምዕ 1-3)፡- ዘማ የሆነችው የሆሴዕ ሚስት ታሪክና ምሳሌያዊ ትርጉም

2. (ከምዕ 4-14)፡- በሕዝቡና በካህናቱ በነገሥታቱም ላጁ ስለተ□ረቱ□ □ቀሳ

ቸ. ትንቢተ አሞጽ

አሞጽ የሚለው የሥሙ ትርጓሜ የተለያየ አተረጓጐም ቢኖረውም ኢትዮጵያውያን

ሊቃውንት /የብሉይ ኪዳን/ አሞፅ ማለት ፅኑ□በእግዚአብሔር ማለት ነ□ ሲሉ ይፃል□ታል፡፡ በሌላ አተረጓጐም እግዚአብሔር ይሸከማል ወይም ይደግፋል ማለት ነውም ይላሉ፡፡ ይህ አሞጽ ትውልዱ ከነገደ ስምዖን እንደሆነ አባቱ ቴና እናቱ ሚስታ□እንደሚባሉ ሲነገር በይሁዳ ውስጥ በተቁሔ /ቲቶ/ በተባለችው ከተማ ይኖር ነበር፡፡ አሞጽ ላም ጠባቂና የዋርከ ፍሬ ለቃሚ ነበር፡፡ (አሞ 1÷1፣7÷1ወ) አሞጽ በክለታዊ ተፅባሩ ተሰማርቶ□ሳለ ለሰሜኑ ሕዝብ ነቢይ እንዲሆን እግዚአብሔር ጠራው፡፡/አሞ 7÷1ወ15/ አሞጽ ትንቢት መናገር የጀመረው በይሁዳ ንጉሥ በአዝያን ዘመነ መንግሥት ነበር፡፡

ትንቢተ አሞጽን የጻፈው ራሱ ሲሆን ከ783-743 ቅ.ክ በኢየሩሳሌም ሳለ እንደጻፈው ይተረከል፡፡ ትንቢተ አሞጽ 9 ምዕራፎች ያሉት የትንቢት መጽሐፍ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

የፍርድን ቃል በሰፊው ይዘግባል፡፡ መጽሐፉ በመጨረሻ ላይም በፍጻሜ ዘመን ላይ ለእስራኤል ሆነ ለአሕዛብ የደኅንነትና የሰላም ጊዜ እንደሚመጣ የአዲስ ኪዳንን ዘመን በትንቢት ያመላክታል

አከፍ□ሉ፡-

1. (ምክ 1-2)፡- በእስራኤልና በእስራኤል ጐረቤት ሀገሮች የእግዚአብሔር ፍርድ □እንደሚደረግ ይገልጻል
2. (ምክ 3-6)፡- □እስራኤል ሕዝብ የተደረገለትን የንስሐ ጥሪ ባለመቀበሉ ከላይ የተገለጸው የትንቢት ቃል ተግባራዊ እንደሚሆን ማረጋጫ ሰጥቷል
3. (ምክ 7-9)፡-እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስለሚያመጣው ፍርድ፣ ነቢዩ ያያቸው ራዕዮችና በፍጻሜ ዘመን ስላለው ተስፋ ይተርካል

ኀ. ትንቢተ ሚክያስ

ሚኪያስ ማለት መኑ ከመ አምላክ ትርጉሙም እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው? ማለት ሲሆን በፍልስጤም ውስጥ በምትገኘው የጌት አነስተኛ ከተማ በነበረችው በሞሬታዊ የተወለደ ሰው ነው፡፡

ሚኪያስ በነቢይነት ያገለገለበት ዘመንም በይሁዳ ነገሥታት በኢዮአታምና በአካዝ በሕዝቅያስም ዘመነ መንግሥት ሲሆን የኢሳይያስም የዘመን ጓደኛ ነበር፡፡ ሚኪያስ በትምህርቱ ተቀባይነት ያለው ሲሆን በተፊ ማሪም በነቢይነቱ የታወቀ አባት ነበር፡፡

ነቢዩ ሚኪያስ በ700 ዓ□ ቅ.ክ በኢየሩሳሌም □ጸፈው መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ 7 ምዕራፎችን ጁ□ል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ ባቢሎን ምርኮ ነቢያቱን ካህናቱን መኳንንቱን ይዞ□ል። ስለ አምልኮ ሥነ ሥርዓት፣ ስለ ፍቅር፣ ስለርህራሄ፣ ስለትህትና፣ ስለመሲህ መምጣትና አድኅኖት ይተርካል።

አከፍ□ሉ፡-

1. (ከምዕ 1-2)፡- እስራኤልና ይሁዳን የሚመለከቱ ትንቢቶች
2. (ከምዕ 3-5)፡- ስለ ፍትሕና እና አድኅኖት /ማዳን/ ይተርካል
3. (ከምዕ 6-7)፡- ስለ ሕዝቡ ቅጣትና የእግዚአብሔር ፍጹም ምሕረት ይገልጻል

ነ. ትንቢተ ኢዩኤል

ኢዩኤል ማለት እግዚአብሔር አምላክ ነው ማለት ነው። ኢዩኤል ያገለግል የነበረው በይሁዳ መንግሥት ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አገልግሎት የመጣበት ምክንያት ሕዝቡ ላይ ሊወርድ ስላለው የአንበጣ መንጋ ጾምና ጸሎት ይደረግ ዘንድ ሕዝቡን□እንዲያስጠነቅቅ ነው።

ትንቢተ ኢዩኤል በነቢዩ ኢዩኤል ከጌታ ልደት 600 ዓመት በፊት የተጻፈ መጽሐፍ ሲሆን ሦስት ምዕራፎችንም አካቷል።

የመጽሐፉ ይዘት

የሚመጣውን ድኅነትና የጠላቶቻቸውን መደምሰስ ጹፏል□ል። ስለመንፈስ ቅዱስና ሕዝቡ ወደ አምላካቸው እንዲመለሱ ይናገራል።

አከፍ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- ስለ አንበጣ መንጋ□እና በንስሐ ስለመመለስ
2. (ምክ 2)፡- ንስሐ እንዴት□እንደሚገባ እና መንፈስ ቅዱስ በኋላኛው ዘመን መውረድ
3. (ምክ 3)፡-□ማጁታዘዙት እንደሚቀጡ ለታዘዙት ደግሞ በረከት □እንደሚሰጣቸው ይተርከል።

ኘ. ትንቢተ አብድዩ

የስሙ ትርጓሜ ገብረ እግዚአብሔር (የእግዚአብሔር አገልጋይ) ማለት ነው። በዕብራይስጡ አጠራር ደግሞ አባድያህ ይባላል። አብድዩ ነብየ ይሁዳ ሲሆን ትንቢት ይናገር የነበረው ግን በሙት ባሕር ደቡብ በምትገኝ ጥቂት ሕዝቦች በሚኖሩበት በኤዶምያስ ምድር ነበር። ኤዶምያስም ትንሽ ሀገር ስትሆን በዚህች ሀገር ይኖሩ የነበሩት የኤሳው ዘሮች ናቸው።

ትንቢተ አብድዩ በነብዩ አብድዩ □ተ□□ 1 ምክራአና 21 ቁጥሮች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

- ኤዶምያስ በይሁዳ ላይ ስለማመጽ
- ስለ ትዕቢቷና በዚህ ምክንያት ስለሚያገኛት ውርደት

- ስለሚመ□□· □እግዚአብሔር የፍርድ ቀን ይናገራል
- ስለ እስራኤል ደኅንነትና ስለመንግሥተ እግዚአብሔር ይናገራል

አከኛ□ሉ፡-

1. (ከቁ 1-9)፡- ኤዶምያስ በትዕቢቷ እንደምትጠፋ
2. (ከቁ 10-14)፡- ኤዶምያስ በኢየሩሳሌም ውድቀት መደሰቱ ትክክል እንዳልሆነ ይገልፃል፡፡
3. (ከቁ 15-21)፡- □እግዚአብሔር ቀን በአህዛብ ላይ እንደሚመጣና የእግዚአብሔር ተስፋ መንግሥት በይሁዳ እንደሚመሰረት ያመለክታል፡፡

ሀ. ትንቢተ ዮናስ

ዮናስ ማለት ርግብ ማለት ነው፡፡ በዕብራይስጥ ዮናህ ሲባል በላቲኑም ጆናስ ይባላል፡፡ ዮናስ በባቢሎን ውስጥ በምትገኘ□· በጋትሔድር □ሚኖር ሰው ሲሆን አባቱ አማቴ ይባል ነበር፡፡ (ኢያ 19÷1ወ 13)፣(ዮና 1÷1) የቤተክርስቲያናችን የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ዮናስ በሰራኘታ□ ትኖር የነበረችው መበለት እናቱ እንደሆነች ሕፃኑም ሞቶ ኤልያስ እንዳስነሣውና የኤልያስ ደቀመዝሙር በመሆኑ ከኤልያስ ጋር ሳለ ሀብተ ትንቢት እንደተሰጠው ያስረዳሉ፡፡ (1ኛ ነገ17÷17-23)

ዮናስ ትንቢት የተናገረው በአሞራውያን ዋና ከተማ በነነዌ ነበር፡፡ ትንቢተ ዮናስ 4 ምዕራፎች ያሉት በነቢዩ ዮናስ የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ለየት የሚያደርገው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ስለ ጸሐፊው ነቢዩ ታሪክ የሚተርክ በመሆኑ ነው፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

እግዚአብሔር የእስራኤል ብቻ ሳይሆን የአሕዛብ አምላክ እንደሆነና በንሰሐ ወደ እርሱ የተመለሱትን ሁሉ በምሕረት እንደሚጐበኝ ማሳየት

አከኛ□ሉ፡-

1. (ከምክ 1÷1-3)፡- እግዚአብሔር ለዮናስ የሰጠው ትዕዛዝና የዮናስ ትንቢት
2. (ከምክ 1÷4-12)፡- የዮናስ መሸሸና የእግዚአብሔር ክትትል
3. (ምክ 2)፡- ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ውስጥ ሳለ ያሰማው ጸሎትና ወደ ቀድሞ ጥሪው መመለሱን ይገልጻል
4. (ከምዕ 3÷1-9)፡- እግዚአብሔር ለሁለተኛ ጊዜ ለዮናስ የሰጠው ትዕዛዝ
5. (ከምዕ 3÷1ወምክ 4÷11)፡-እግዚአብሔር ለሕዝቡ ባሳጸ□· ምሕረት ዮናስ ባለመደሰቱ እንደተገሰ□ ይናገራል፡፡

ከ. ትንቢተ ናሆም

ናሆም ማለት መጽናናት ወይም ዕረፍት ማለት እንደሆነ ልዩ ልዩ መዛግብት ያስረዳሉ። የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ናሆም ማለት ፈውስ፣ ፈውሰ እግዚአብሔር ማለት ነው ሲሉ የተረጐሙ ሲሆን እናቱም ሶስና እንደምትባል ያስረዳሉ። የናሆም የትውልድ ቦታ አልቆሽ ይባላል (ናሆ 1÷1)

ትንቢተ ናሆም የነነዌን ውድቀት ይናገራል። ናሆም ከነነዌ ውድቀት በፊት ማለትም ከ612 ቅ.□ ጥቂት ቀደም ብሎ በትንቢት አገልግሎት ላይ እንደነበረ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ያስረዳሉ።

ትንቢተ ናሆም የተጻፈበት ዘመን ከ621-612 □ዓ ባለው ጊዜ ሲሆን ጸሐፊውም ራሱ ናሆም ነው። በኢየሩሳሌም ሳለ እንደጻፈው ይነገራል። ትንቢተ ናሆም 3 ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

የመጽሐፉ ዋና መልዕክት በቀል የእኔ ነው በሚለው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት

□እስራኤል ሕዝብ ጠላት የነበረችውን ነነዌን ከጥፋት ከተመለሰች በኋላ ባሳየችው ጭካኔ እግዚአብሔር የሚበቀላት መሆኑን ነው።

አከኛ□ሉ፡-

1. (ምክራአ 1)፡- እግዚአብሔር የፍርድ የበቀል አምላክ ስለመሆኑ
2. (ምክራአ 2)፡- በ3 ዓበይት ድርጊት የተፈጸመ ቅጣት
3. (ምክራአ 3)፡- ነነዌ የጠፋችበት ምክንያት ምን ስለመሆኑ ይተርካል

ሽ. ትንቢተ ዕንባቆም

ዕንባቆም ማለት እቅፍ ወይም የሚያቅፍ ማለት ነው የሚሉ ሊቃውንት ሲኖሩ አንዳንዶች

ደግሞ ተክል ማለት ነው ይላሉ። የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ደግሞ ዕንባቆም ማለት ታቢብ ማእምር □ለባዊ ማለት ነው ሲሉ ተርጉመውታል።

ዕንባቆም ከሌዊ ወገን የሆነ የኢያሱ ልጅ ነው የሚሉ አሉ። በተጨማሪም ነቢዩ ዳንኤል ወደ ባቢሎን ተማርኮ ሳለ ዕንባቆም ለአጫጆች ምሳ ይዞ ሲሄድ የእግዚአብሔር መልአክ በነገረው መሠረት ወደ ባቢሎን በመሄድ ለዳንኤል ምግብ እንዳቀረበ ተጽፏል። በ□ህ ታሪክ መሠረት ዕንባቆም □ዞ□ኑ ኔ□ዳ እየተባለ ከሚጠራው /586 ቅ.ል.ክ/ ምርኮ በፊት እንደነበር መረዳት ይችላል።

ትንቢተ ዕንባቆም ከጌታ ልደት 600 ዓመት በፊት በነበዩ ዕንባቆም □ዙ□□ ሦስት ምዕራፎች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

እግዚአብሔር ክፋት ሲበዛ እንደሚታገስ ክፋዎች ለጊዜው ቢታገሳቸውም ግን ኋላ □እንደሚያጠፋቸው እንዲሁም ጻድቅ በእምነቱ እንደሚድን ይገልጻል።

አከኛ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- ነቢዩ ኅጢአት በመብዛቱ ወደ እግዚአብሔር እንደጸለየና □እግዚአብሔርም በባቢሎናውያን መሣሪያነት ቅጣት□እንደሚያመጣ ተጽፏል
2. (ምክ 2)፡- አምስቱ የዋይታ ቃላት
3. (ምክ 3)፡- የዕንባቅም ጸሎትና ምስጋና እንዲሁም ተማጽኖ ተጽፏል

ወ. ትንቢተ ሶፎንያስ

ሶፎንያስ በምድረ ይሁዳ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ የነበረው የቤተ መንግሥት ወገን ሲሆን የስሙ አጠራር በዕብራጅስዓ ጴፋንያህ ጁባላል። □ስሙ ትርጉም በሁለት መልኩ ተገልጿል። በተለያዩ መዛግብት ተጽፎ እንደሚገኘው ከደኖ/ሠወሮ/ እፅ□እ□(እግዚአብሔር ይከልላል □ጁም ጁታብቃል) ማለት ሲሆን በሌላ ትርጓሜም ሰፋኒ -ቹር፣ ቀ□ሲ -አመስጋኝ፣ ሥሉጥ-የሠለጠነ ማለት እንደሆነ ያትታሉ።የነቢዩ ሶፎንያስ አባት ኩሲ እናቱም ንህባ እንደሚባሉ የኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን ሊቃውንት ይተርከሉ። በነቢይነት የተጠራውም በ20 ዓመቱ በኢዮስያስ ዘመን መንግሥት እንደሆነ ይተርከል።

መጽሐፉን እራሱ ሶፎንያስ በ700 ዓ□ ቅ.ል.ክ በኢየሩሳሌም □□ታል ሥስት ምዕራፎች አሉት።

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ እግዚአብሔር የቁጣ ቀን፣ ስለ ምርኮ፣ ክፉ አድራጊዎችን ስለመገሰጽና ከምርኮ ስለመመለስ ይናገራል።

አከኛ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- በኅጢአታቸው ምክንያት ሕዝቡ ላይ ስለሚመጣው ቁጣ፣ ጥፋቱን አምኖ የተጸጸተ ደግሞ ምሕረትን እንደሚያገኝ
2. (ምክ 2÷1-3)፡- አይሁድ ንስሐ እንዲገቡ የቀረበላቸው ጥሪ
3. (ከምዕ 2÷4-15)፡- የአይሁድ ጎረቤቶች በአይሁድ ላይ በደል በመፈጸማቸው □እግዚአብሔር □እንደሚበቀላቸው
4. (ምክ 3)፡- በኋላኛው ዘመን አረማውያን ወደ እግዚአብሔር እንደሚመለሱ ይተርካል።

ዘ. ትንቢተ ሐጌ

ሐጌ ማለት በዓላዊ፣ በዓልየ፣ ዘተወልደ በዕለተ በዓል ማለት ነ□። እስራኤላዊያን እፀዕ በ□መቀ ሁኔታ ከሚያከብሯቸው በዓላት በአንዱ ማለትም በቂጣ በዓል፣ በሰባቱ ሱባኤ በዓል፣ በዳስ በዓል መወለዱን ያመለክታል። (□□ 16÷16) ነቢዩ ሐጌ ከህፃንነቱ ጀምሮ ለነቢይነትና ለክህነታዊ አገልግሎት የተጠራ ሲሆን የተወለደውም በምርኮ በባቢሎን ሀገር ነው። ሐጌ በቂሮስ ትዕዛዝ ከምርኮ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱት ምርኮኞች ጋር ወደ ኢየሩሳሌም የመጣ በጎ አገልጋይ ነው።

ከምርኮም ከተመለሰ በኋላ የፈረሰውን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ለማሠራት ከአዶ ልጅ ከዘካሪያስ ፉር በመሆን ህዝቡን በማስተባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል።(ዕዝ 6÷14) «በውኑ ይህ ቤት ፈርሶ

ሳለ እናንተ ራሳችሁ በተሸለሙ ቤቶቻችሁ ለመኖር ጊዜው ነውን?» (ሐቴ 1÷4) በማለት ሕዝቡን ለቤተመቅደሱ ሥራ ያነሣሳ የነበረ ታላቅ ነቢይ ነበር።

ይህንን የትንቢት መጽሐፍ ነቢዩ ሐጌ በ500 ዓ□ ቅ.ል.ክ በባቢሎን ምርኮ ሳለ ጽፎታል □ሚሉ ሊቃውንት አሉ። ትንቢተ ሐጌ ባለ 2 ምዕራፎች መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

ከሁሉ በፊት የእግዚአብሔር የሆነውን እንዲያስቀድሙ ማሳሰብ እና ቤተመቅደሱን □እንዲሠሩ ማበረታት ነው።

አከኛ□ሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- ቤተመቅደሱን ለመሥራት እንዲነሡ ነቢዩ የተናገረውን መልዕክት ይዟል
2. (ከምክ 2÷1-9)፡- ቤተመቅደሱን ለሚሠሩ ሰዎች ቤተ መቅደሱን ከፊተኛው በወርቅና በ□ብቱ ቢያንስም በመንፈሳዊ ጌጡ እፀፅ ጸማረ እንደሆነና በሥራውም ከእነርሱ ጋር መሆኑን ይገልጻል
3. (ከምዕ 2÷1ወ19)፡- እግዚአብሔር ለሕዝቡ የተናገረውን የተስፋ ቃል ይገኝበታል
4. (ከምክ 2÷2ወ23)፡-ለ□ዙባቤል እግዚአብሔር ከፍ እንደሚያደርገው ጠላቶቹንም እንደሚያዳክምለት የሚገልጽ የትንቢት ቃል ይገኝበታል

ዝ. ትንቢተ ዘካርያስ

□ካሪያስ በክብራጁስጥ □ካሪያህ □ሚባል ሲሆን ትርጉሙም ዝኩር እግዚአብሔር ማለት ነው። ወደ አማርኛ ስንመልሰውም እግዚአብሔር ያስታውሳል ማለት ነው። ነቢዩ ዘካሪያስ የሐጌ የዘመነ ትንቢት ጃ□ኛ ነው /ዕዝ 5÷1/ አነሣሱ ግን ሐጌ በሁለት ወር እንደሚቀድም ይተርካል። ይህ ነቢይ አገልግሎቱን የጀመረው በወጣትነቱ ሲሆን በቀዳሚ ዳርዮስ በ2ተኛ ዓመተ መንግሥቱ የነቢይነት ተልዕኮውን ጀምሯል።

ነቢ□ □ካሪያስ መጽሐፉን በባቢሎን ምርኮ በ500 ዓ□ ቅ.ል.□ እንደፃፈው ይታወቃል። ትንቢተ ዘከሪያስ 14 ምዕራፎችን የያዘና በ4 ዐበይት ክፍሎች የተከፈለ የትንቢት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

የሐጌን ትምህርታዊ ማስጠንቀቂያ የራሱንም መልዕክት በሰፊው ያቀረበና ሐጌ የዘረዘራቸው በሕዝቡ ላይ የደረሱ ችግሮች የሚወገዱት ሕዝቡ በንስሐ ሲመለስ እንደሆነ ይተርካል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- ወደ አምላካቸው እንዲመለሱ ያስጠነቅቃል
2. (ከምዕ 2-6)፡- ስምንት ራዕዮችን ይዟል(ከም 7-1ወ)፡- ሁለተኛ ራዕይ 4 ቀንዶች 5 ጠራቢዎች

3. (ከምዕ 11-14)፡- ስለ □ም፣ ስለ ጌታችንና ስለቅዱሳን ሐዋርያት ይገልጻል፡፡

የ. ትንቢተ ሚልክያስ

ሚልክያስ ማለት መልዕክተኛዬ ማለት ነው፡፡ ትንቢተ ሚልክያስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ470 እና በ440 ዓመት መካከል በኢ□ሩሳሌም የተነገረ ቃለ ትንቢት ነው፡፡ ዘመኑም በዕዝራን እና በነህምያ ዘመነ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በነቢዩ ሚልክያስ ሲሆን 4 ምዕራፎችም አሉት፡፡

የመጽሐፉ ይዘት

□እስራኤልን ኃጢአትና ክህደት እንዲሁም በኃጢአተኞች ላይ የሚመጣውን ቅጣት □እንዲሁም ስለጌታችን ይናገራል፡፡

አከኛ□ሉ፡-1. (ከምዕ 1-3)፡- በጥያቄና መልስ የቀረበ መልዕክት

2 (ምክ 4)፡- እግዚአብሔርን የሚፈሩ በፍርድ ቀን ተጠብቀው እንደሚኖሩ ይናገራል፡፡

ምዕራፍ ሦስት

የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት

ሐዲስ ኪዳን ማለት አዲስ ውል አዲስ ስምምነት ነው፡፡ ሐዲስ ኪዳን የሚለው ቃል ከዚህ ኪዳን በፊት ሌላ ኪዳን እንደነበረ የሚያስረዳና የቀደመውን መንደርደሪያ አድርጎ የተነሣ አዲስ ስምምነት እንደሆነ ያስረዳል፡፡ (ኤር 31፥31) ይህ ኪዳን እግዚአብሔር እስራኤል ዘነፍስ ከተባሉት ክርስቲያኖች ጋር የተዋዋለው ስምምነት (ኪዳን) ነው፡፡

የሐዲስ ኪዳን ዘመን የሚባለው ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከ እመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ለድኅነተ ዓለም ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለምእመናን ለመስጠት የተዋዋለበት ዘመን ነው፡፡ (ማቴ 26፥26) በዚህ ዘመን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱሳን ሐዋርያትና አርድእት የተሰጡ ትምህርቶች የተጻፉ መጽሐፍት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ይባላሉ፡፡ ጸሐፊዎቹ በጌታችን የተመረጡ ሐዋርያት እና አርድእት ናቸው፡፡ (1ኛዮሐ 1፥11)፣(2ኛጴጥ1፥21) ይህ ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስ ዐበይት ክፍላት አንዱ ነው፡፡ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉበት ዘመን ከ 45-100ዓ.ም ባለው ጊዜ ሲሆን የመጻሕፍቱ ቁጥርም 35 ነው፡፡

እነዚህ መጻሕፍት አቀራረብ በታሪክ በትምህርት ወይም በትንቢት መልክ ቢሆንም ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚተርኩ ስለሆነና ማዕከላቸው እርሱ ስለሆነ በጥቅሉ ወንጌል ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ፡፡ ከዚህም ሌላ የሐዲስ ኪዳን ዘመን ለብሉይ ኪዳን ዘመን ፍጻሜ ስለሆነ በዘመነ ብሉይ የተነገሩ ምሳሌዎችና ትንቢቶች በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጠቅሰው ፍጻሜያቸውንና ትርጉማቸውን አግኝተዋል፡፡

የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አከፋፈል

እንደ ብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁሉ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአምስት ዐበይት ክፍሎች ከፍለን መመልከት እንችላለን ::

1. የወንጌል ክፍል
2. የታሪክ ክፍል
3. የሥርዓት ክፍል
4. የመልዕክት ክፍል
5. የትንቢት ክፍል

1. የወንጌል ክፍል

ወንጌል የሚለው ቃል የግሪክ ሲሆን ኢቫንጌልዮን (evangelion) ከሚለው ቃል የተገኘ ነው፡፡ ትርጉሙም ብስራት፣የምስራች፣ስብከት ማለት ነው፡፡ ወንጌል ደስ□ የምስራች የሚገለጥበት ቋንቋ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደነገሠ ዲያብሎስ እንደተዋረደ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም እንደተወለደ ስለ ሰ□ ኀጢአት ሞቶ እንደተነሣ ያበስራልና፣ ሞተ ሥጋ ወነፍስ እንደጠፉ ሕይወተ ሥጋ ወነፍስ እንደተስፋፋ ይናገራልና እንዲህ የሚል ስያሜ ተሰጠው፡፡

በቤተክርስቲያን ታሪ□ □ታወቁትና የታመኑት አራት የወንጌል መጻሕፍት ብቻ ናቸው፡፡ ጸሐፊዎቹም ከሐዋርያት ቅዱስ ማቴ- ስና ቅዐ ስ ዮሐንስ ሲሆኑ ከአርድዕት ወገን ደግሞ ቅዐ ስ ማርቆስ እና ቅዱስ ሉቃስ ናቸው፡፡ ወንጌል በአራት ክፍል ሆኖ መጻፉ ዓለም በአራቱም ማዕዘን ጸንታ በአራቱ □ኤለ ዘመን ተመስላ በአራቱ መገብተ አውራኃ ከዋክብት ተመርታ እንደምትኖር ያስገነዝባል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ አራት የወንጌል መጻሕፍት ይገኛሉ፡፡ እነርሱም ፡-

ሀ. □ማቴዎስ ወንጌል

ለ. **የማርቆስ ወንጌል**

ሐ. **የሉቃስ ወንጌል**

መ. **የዮሐንስ ወንጌል**

በጸሐፊዎቹ ስም መጽሐፎቹ መጠራታቸው ጸሐፊዎቹን ለማሳወቅ እንጂ ወንጌሉ የጌታችን □መትኅኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ መጽሐፍቱን በጸሐፊዎቹ ስም የሰየሙት 318ቱ ሊቃውንት ናቸው፡፡ አራቱም ወንጌላት የሚተርኩት ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቢሆንም በአገላለጥ ወይም በይዘት አንዱ ከአንዱ ይለያያል፡፡ □ማቴ- ስ □ማርቆስ እና የሉቃስ ወንጌሎች በብዙ ምዕራፍ የሚመሳሰሉ ቢሆንም ማቴዎስ የክርስቶስን መሲህነትና ትምህርት ማርቆስ ተአምራቱንና ትምህርቱን ሉቃስ ስለሴቶች ስለችግረኞች ስለ ጌታችን ሰብአዊ ርኅራኄ ጸሰረ□ሉ፡፡ ዮሐንስ ግን ተለይቶ ከጌታ ምትራዊ ልደት አንሥቶ ረቀቅ ያለውን ምስጢረ መለኮትን ይገልጻል፡፡

ሀ. **□ማቴዎስ ወንጌል**

ማቴ- ስ ከ12ቱ ሐዋርያት አንዱ ነው፡፡ በ4ቱ የሐዋርያት ዝርዝሮች በዚህ ስም ሲታ□ቅ በማቴ- ስ ወንጌል ብቻ ቀራጭ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶት ይገኛል፡፡ (ማቴ 10፥3) ማርቆስና ሉቃስ ሌዊ ብለው

በቤተሰቡ ስም ይጠሩታል፡፡ የአባቱ ስም እልፍዮስ (ዲቁ) ሲባል እናቱ ክሩትስያ ትባላለች፡፡ (ማር 2፥14) ጌታ ሲጠራው በቀራጭነት ሥራ ላይ ነበር፡፡ ነገር ግን ሁሉን ተወ፤ በቤቱም ግብዣ አደረገ፡፡ (ማቴ 9፥9-13) ማቴዎስ ቀራጭን እንኳን በሚመርጥ በእግዚአብሔር ጸጋ እየተደነቀ መላ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ሐዋርያ ነው፡፡

ሐ□ርጸ□· ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ለአይሁድ ዕብራውያን በፍልስጤም ምድር በ41 ዓ.ም አካባቢ ሲሆን ወንጌሉን ስለጻፈበት ቋንቋ ሦስት ዓይነት ግምቶች አሉ፡፡ ዕብራይስጥ አረማይክና ግሪክ ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያት፡-

1. **አይሁድ ለጠየቁት ጥያቄ ለመመለስ**
2. **ቄታችን የአብርሃም □ና የዳዊት ዘር ስለመሆኑ ለመግለጽ**
3. **ቄታ ነቢይ ሳይሆን አምላክ ነቢያት መሆኑን ለመግለጽ**
4. **ትንቢተ ነቢያት በጌታችን መፈጸሙን ለማስረዳት**

አከፋፈሉ፡- በምዕራፎች ብዛት የመጀመሪያ ወንጌል ሲሆን 28 ምዕራፎችን አካቷል፡፡

1. **(ከምዕ 1-2)፡- ስለጌታችን የዘር ሐረግ ልደት□እና ስደት**
2. **(ከምዕ 3፥4-11)፡- ቄታችን ማስተማር ከመጀመሩ በፊት ስለነበሩ ታሪኮች**
3. **(ከምዕ 4፥12- ምክ 25)፡- □ቄታችን ትምህርቶች**
4. **(ከምዕ 26-27)፡- ቄታችን መከራ መቀበሉና መሞቱን**
5. **(ከምዕ 28፥1-20)፡- ስለቄታችን ትንሣኤ ይናገራል፡፡**

ለ. የማርቆስ ወንጌል

በአይሁድ ዘንድ ስሙ ዮሐንስ ሲሆን በሮማውያን ማርቆስ ይባላል፡፡ አባቱ አርስጦቦሎስ እናቱ ደግሞ ማርያም ትባላለች፡፡ (□ሐ 12፥12) ቤትዋ በኢየሩሳሌም ነበር፡፡ ምዕመናንም ለጸሎት በቤትዋ ይሰባሰቡ ነበር፡፡ (ሐ□ 12፥12-17) አጎቱ በርናባስ እና ጳውሎስ ለስብከት ሲጓዙ ማርቆስ ያገለግላቸወ ነበር፡፡ (ቆላ 4፥10) (ሐ□ 12፥25) □እስክንድርያ ቤተክርስቲያን እንደመሠረተ አበው ይናገራሉ፡፡ እስከአሁንም □እስክንድርያ ቤተክርስቲያን አባት ይባላል፡፡

ከሰባ ሁለቱ አርድዕት መከከል የሆነው ቅዱስ ማርቆስ ወንጌሉን የጻፈው በ44 ዓ.ም ለሮማውያን በሮም በሮማይስጥ ቋንቋ ነው፡፡ ቅዱስ ማርቆስ የላቲን የግሪክ እና የዕብራይስጥ ቋንቋን የሚያውቅ ሲሆን ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያትም ሮማውያን በዘመናቸው ገናና እኛ ብቻ ነን በማለት ይናገሩ ነበርና የጌታችን ገናና ጎያልነት ተአምራቱን ለመግለጽ ጽፎላቸዋል፡፡

አከኛ□ሉ፡-የማርቆስ ወንጌል በምዕራፎች ብዛት አጭሩ ሲሆን 16 ምዕራፎችን ይዟል፡፡4 ዐበይት

ክፍሎችም ይኖሩታል፡፡

1. **(ከምዕ 1፥1-13)፡- ቄታችን ከማስተማሩ በፊት ያደረጋቸው ነገሮች**
2. **(ከምዕ 1፥14 - ምክ 10)፡- ቄታችን በገሊላ አውራጃ ስለማስተማሩ**
3. **(ከምዕ 11፥13)፡- ቄታችን ኢየሩሳሌም ገብቶ □ንዳተማረ**
4. **(ከምዕ 14፥16)፡- ስለ ቄታ መከራ ሞት ትንሣኤ እና ዕርገት ይናገራል**

ሐ. **የሉቃስ ወንጌል**

የስሙ ትርጉም መብራት፣ □ቃቤ ሥራጁ፣ ትንሣኤ መበስር ማለት ነው። ቅዱስ ሉቃስ ሀኖ አንጾክያ ቁዓሩም ከ72ቱ አርድዕት ነው። ቅዱስ ሉቃስ ልዩ የሆነ የሥነ ሥዕል ችሎታ□ ነበረው። ይህንም በወንጌሉ እና የሐዋርያት ሥራ መጽሐፉ ሥዕላዊ አገላለፅ በመጠቀም አሳይቷል። ቅዱስ ሉቃስ ተ□□ፀ እና ታማኝ የጳውሎስ ደቀመዝሙር እንደነበረ በሕክምናም እንዳገለገለው ይናገራል። (2ኛ ጢሞ 4፥11)

ቅዱስ ሉቃስ ወንጌሉን ከ58-60 ዓ.ም በግሪክ ቋንቋ ቴዎፍሎስ ለተባለ ለግሪክ ባለስልጣን የጻፈው ሲሆን የጻፈበትም ምክንያት በቃል የተማረውን የክርስቶስን ነገር በሚገባ እንዲያውቅ ለማድረግ ነ□።

አከፍ□ሉ፡- ወንጌሉ 24 ምዕራፎችን ሲይዝ 6 ዓበይት ክፍሎችም አሉት

1. **(ከምዕ 1-2)፡- □ዜታችን ታሪክ ከጽንሰቱ □ስከ ልደቱ**
2. **(ከምዕ 3፥1 - ምዕ 4፥13)፡- ዜታችን የማስተማር አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት ያለው ታሪ□**
3. **(ከምዕ 4፥14 - ምክ 9)፡- ዜታችን ሕዝቡን ስለማስተማሩ □ና ስለመፈወሱ**
4. **(ከምዕ 10፥1 - 18፥30)፡- ጌታችን ወደ መስቀል ያደረገው ቱዞ**
5. **(ከምዕ 18፥31 - ምክ 23)፡- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀል**
6. **(ከምዕ 24፥1-53)፡- ስለ ዜታ ትንሣኤ እና እርገት**

መ. የዮሐንስ ወንጌል

ዮሐንስ ማለት እግዚአብሔር ጸጋ ነው ማለት ነው። የያእቆብ ወንድም የዘብድዮስ ልጅ (ማቴ 4፥21) እናቱም ሰሎሜ እንደሆነች ይገመታል። ወላጆቹ ሃብታሞች ነበሩ። ዓሣ በማጥመድ ላይ ሳሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጠራው። ጌታችን ይወደው የነበረና የምስጢር ሐዋርያት ከሚባሉት መካከል አንዱ ነበር። በወንጌሉ ላይ ስሙ አልተጠቀሰም። ነገር ግን ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀመዝሙር እያለ ራሱን ይገልጻል።

ወንጌሉ ከትረካ ይልቅ ነገረ መለኮታዊ ይዘት ያለው ነው። ዮሐንስ ከፍጥሞ ደሴት ግዞት ሲመለስ በ96ዓ.ም አካባቢ በኤጂያን ባሕር ወደብ በዮናኒ (በጽርዕ) ቋንቋ ለኤፌሶን ምዕመናን ወንጌሉን ጽፎላቸዋል። ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያት ሰው ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት አምኖ እንዲድን ይመጣል የተባለው መሲህ ክርስቶስ መሆኑን ለመግለጽ፤ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑን ለማስረዳት ነው።

አከፋፈሉ፡- የዮሐንስ ወንጌል 21 ምዕራፎች ሲኖሩት 4 ዐበይት ክፍሎችም አሉት፡-

1. (ከምዕ1፥1-18)፡- ጌታችን በቅድምና ስለመኖሩ እና በሥጋ ማርያም ስለመገለጡ
2. (ከምዕ1፥19 - ምዕ 12)፡- ጌታችን በማስተማር ዘመኑ ያደረጋቸው ነገሮች
3. (ከምዕ 13-17)፡- ጌታችን ከደቀመዛሙርቱ ጋር እና በመጨረሻ ያደረጋቸው ነገሮች
4. (ከምዕ 18- ምዕ 21)፡- የኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀልና ትንሣኤን ይገልጻል።

2. የታሪክ ክፍል

የሐዋርያት ሥራ

ሐዋርያት የሚለው ቃል የሐዋርያ ብዙ ቁጥር ሲሆን ሐዋርያ ሖረ /ሄደ/ ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጓሜውም ሒያጅ፣ ተጓዥ፣ መልእክተኛ ማለት ነው፡፡ ሐዋርያት በጌታችን አማካኝነት ከተመረጡ በኃላ ለጊዜው በምድረ እስራኤል ቀጥሎም በዓለም ዙሪያ እየዞሩ ወንጌልን እየሰበኩ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቀዋል፡፡

ቅዱስ ሉቃስ ታሪኩን የጻፈው በ64/65 ዓ.ም በሮም ሃገር በግሪክ ቋንቋ ሲሆን ታሪኩን ለታኦፌላ (ቴኦፍሎስ) ልኮለታል፡፡ የተጻፈበት ምክንያትም፡-

1. ለታኦፌላ እስከ 34 ዓ.ም ያለውን ገልጾለት ነበርና ቀጣዩን ሊነግረው
2. የቅድስ ቤተ-ክርስርስቲያንን አመሰራረትና ዕድገት ለመግለፅ
3. የርደተ መንፈስ ቅዱስን ሁኔታ ለማስረዳት

አከፋፈሉ፡- 28 ምዕራፎች ሲኖሩት በ5 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላሉ፡፡

1. (ከምዕ 1÷1 - 2÷47)፡- የቤተክርስቲያን መሰረት እና ዕድገት
2. (ከምዕ 3÷1 - 5÷42)፡- የጌታ ደቀመዛሙርት ተግባር ከጰራቅሊጦስ በኃላ
3. (ከምዕ 6÷1-5÷42)፡- በሀገር እስራኤል የቤተ-ክርስቲያን መስፋፋት
4. (ከምዕ 13÷1-11÷16)፡- የቅዱስ ጳውሎስ ታላላቅ ጉዞዎች እና የኢየሩሳሌም ጉባኤ
5. (ከምዕ 21÷17-28÷31)፡- የቅዱስ ጳውሎስ መያዝ እና እስራቱ

3 .የሥርዓት ክፍል

ሥርዓት የሚለው ቃል ሠርዐ ካለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ሕግ፣ ደንብ፣ መርሐግብር ማለት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎቶችን የምትፈጽምባቸው የምታከናውንባቸው እና የምትመራባቸው የሥርዓት መጻሕፍት አሏት፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ሐዋርያት እና ሊቃውንት ቤተክርስቲያን በየጊዜው ለቤተክርስቲያኒቱ መተዳደሪያ ይሆናት ዘንድ በሲኖዶስ የደነገጓቸው ደንቦች ወይም ሕጎች ናቸው፡፡

የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት ቁጥር ስምንት ሲሆኑ የተጻፉበትም ቋንቋ በሱርስት ነው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት ቅዱሳን ሐዋርያት ከዕርገተ ክርስቶስና ከርደተ መንፈስ ቅዱስ በኋላ ተሰብስበው የደነገጓቸው ቀኖናዎች ናቸው፡፡

የሥርዓት መጻሕፍት አከፋፈል

እነዚህ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሦስት ዐበይት ክፍላት ይከፈላሉ

1. መጽሐፈ ዲድስቅልያና አራቱ መጻሕፍተ ሲኖዶሳት
2. ሁለቱ ኪዳናት
3. መጽሐፈ ቀሌምንጦንስ በመባል ይከፈላሉ፡፡

ሀ. መጽሐፈ ትእዛዝ

ትእዛዝ የሚለው ቃል ‹‹አዘዘ›› ካለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን ትርጉሙም ከሥራ አስቀድሞ የሚሰጥ፣ የሚጻፍ፣ የሚነገር ሕግ፣ ሥርዓት ወይም አድርግ አታድርግ የሚል ፈቃድና ደንብ ነው።

መጽሐፈ ትእዛዝ ከ72 አንቀጾች በላይ ሲኖሩት መለያ መጠሪያው ወይም መሪ ምልክቱ ‹‹ረስጠብ›› በመባል ይታወቃል።

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፉ ስለ ሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓተ ሢመት አተገባበር፣ ስለ መሥዋዕት አቀራረብ፣ ስለ ንዋየ ቅድሳት ክብር፣ ስለ ሥርዓተ ጥምቀት፣ ስለ ሥጋወደሙ ክብር ወዘተ ይናገራል።

ለ. መጽሐፈ ግጽው

ግጽው ማለት በቁሙ የታየ፣ የተገለጠ፤ ጉልህ ማለት ነው። የዚህ መጽሐፍ መሪ ምልክት ‹‹ራስጠጅ›› የሚባል ሲሆን ቅዱሳን ሐዋርያት ከጻፏቸውና ከሠሯቸው ስምንት የሥርዓት መጽሐፍ አንዱ እና ሐዋርያት ለቀሌምንጦስ የሰጡት ሁለተኛ መጽሐፍ ነው። መጽሐፈ ግጽው 52 ያህል አንቀጾች ያሉት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ እግዚአብሔር ሕልውና፣ ስለ ምስጢረ ሥጋዌ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ስለማስተማሩና ስለ ሠራቸው ሥራዎች ይናገራል።

ሐ. መጽሐፈ አብጥሊስ

አብጥሊስ ማለት ‹‹ቀኖና›› ማለት ነው። መጽሐፈ አብጥሊስ 82 አንቀጾች ያሉት ሲሆን መለያ መጠሪያው ‹‹ረስጠአ›› (ረስጣ) በመባል የሚታወቅ የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶሳት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት፡-

ስለ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ስለካህናት፣ ስለዲያቆናት እና ምእመናን አጠቃላይ የሥራ ድርሻና መንፈሳዊ ሕይወት እንዲሁም ስለ ምስጢረ ንስሐ አሰጣጥና አተገባበር፣ የትምህርተ ሃይማኖትንና የሥርዓተ ቤቱክርስቲያን አስፈላጊነትና ምንነት የሚያስረዳ ነው።

መ. መጽሐፈ ሥርዓተ ጽዮን

ይህ መጽሐፍ የሐዋርያት ትምህርት ከሚባሉት የሐዋርያት ሲኖዶስ አንዱ ሲሆን ሐዋርያት ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስ ከመውጣታቸው አስቀድሞ በጽርሐ ጽዮን ተሰብስበው የሠሩትና የደነገጉት የቤተክርስትያን ሕግና ትምህርት ነው።

የመጽሐፉ ይዘት:-

መጽሐፉ በውስጡ ስለ በዓለ አስተርእዮ (ኤዲፋንያ)፣ ስለ እሑድ በዓል አከባበር፣ ስለ ገሃድ ጾም ወዘተ ያትታል።

መጽሐፈ ኪዳን

ኪዳን ማለት ውል፣ ስምምነት፣ መሐላ ማለት ነው። መጽሐፈ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከተነሳ በኋላ ከዕርገቱ አስቀድሞ ለቅዱሳን ሐዋርያት ያስተማረውን ትምህርት የያዘ ባለ ሁለት ክፍል መጽሐፍ ነው። እነርሱም መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ እና ካልዕ ናቸው።

ሠ. መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ

ይህ መጽሐፍ ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ከዕርገቱ በፊት ለአስራ አንዱ ሐዋርያት በገሊላ ለአርባ ቀናት ያህል እየተገለጠላቸው ያስተማራቸው እየጠየቁት የመለሰላቸውን ያካተተ ከሥርዓተ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ አንዱ ነው። (መጽ.ኪዳን.ቀዳ1፤ ሐዋ 1፥2-3)

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ 59 አንቀጾች ያሉት ሲሆን ከስምንቱ የሐዲስ ኪዳን የሥርዓተ መጽሐፍት ውስጥ የሚመደብ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

መጽሐፈ ኪዳን ቀዳማዊ በውስጡ ስለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን፣ስለዘወትር ኪዳናት፣ትምህርተ ጎቡአት፣እግዚአብሔር ዘብርሃናት፣ቅዳሴ እግዚእ፣በእንተ ቅድሳት ወዘተ የሚናገር መጽሐፍ ነው።

ረ. መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ

መጽሐፈ ኪዳን ካልዕ እንደ ቀዳማዊው በአንቀጽ የተከፋፈለ ሳይሆን ወጥ ሆነው ከተጻፉ የሐዋርያት የትምህርትና የሥርዓተ መጽሐፍ አንዱ ነው። ወደ ፊት የሚደረጉ ታሪኮች የተጻፈበት መጽሐፍ ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

በዚህ መፅሐፍ ክፍል ጌታችን ስለ ነገረ ምጽአቱ፣ ከምጽአቱ አስቀድሞ ስለሚነሡ የዓለም ነገሥታት፣ ስለሐሳዊ መሲህ አነሣስ ያስተማራቸው ይገኝበታል።(ማቴ24፥1)፣(ራዕ 13፥1)

ሰ. መጽሐፈ ዲድስቅልያ

የቃሉ ትርጉም ትምህርት ማለት ነው። መጽሐፉ ከቅዱሳን ሐዋርያት የሥርዓት መጽሐፍ ክፍል አንዱ ሲሆን 43 አንቀጾችን የያዘና ከ35ቱ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት ዝርዝር ውስጥ አንዱ እና ጥንታዊው ነው። የተጻፈውም ከ120 ዓ.ም በፊት ነው።

የመጽሐፉ ይዘት

ስለ ሰው ልጆች ሕይወትና ሞት ስለ ፍቅረ ሰብእ እና ስለ ፍቅረ እግዚአብሔር፣ ስለ ምስጢረ ጥምቀትና ቁርባን፣ ጾምና ጸሎት፣ ስለ ካህናት ክብርና አገልግሎት፣ ስለ ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ያትታል።

ሸ. መጽሐፈ ቀሌምንጦስ

ቀሌምንጦስ ትውልዱ ሮማዊ የሆነ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀመዝሙር እና የሮማ ሦስተኛ ጳጳስ ነበር መጽሐፉን ከቅዱሳን ሐዋርያት

ተረድቶ የቅዱሳት መጽሐፍትን ዝርዝር ያዘጋጀ (የቅዱሳት መጻሕፍት ቁጥር 81 እንደሆነ) አባት እንደሆነ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት በመጽሐፍታቸው ይመሰክራሉ፡፡

ይህ መጽሐፍ ከ81ዱ የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት የሚቆጠር ሲሆን የመጽሐፉን ምስጢር ከጌታ እየተነጋገረ የተረዳው ቅዱስ ጴጥሮስ ነው፡፡ ቀጥሎ ቅዱስ ጴጥሮስ ለደቀመዝሙሩ ለቀሌምንጦስ እየነገረው በመጻፉ በጸሐፊው ስም መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ተብሏል፡፡

የመጽሐፉ ይዘት:-

የመጽሐፉ ይዘት ሥርዓተ ቅዳሴያዊ ቀኖና እና ቅርጽ ያለው ነው፡፡ ስለ ሥርዓተ ቅዳሴያዊ

ቅርጹን አስመልክቶ ስለ ጽላተ ኪዳን ቡራኬ ማለትም በኤጲስ ቆጶስ ቤተ መቅደስ የሚባረክበትን ሥርዓት፣ ሥርዓተ ጥምቀትና በእጅ መንሻና መተያያ ጥምቀት እንደማይፈቀድ፣ ስለ ሥርዓተ ቁርባን ወዘተ ይናገራል፡፡ በቀኖናዊ ክፍሉም ስለ ሰማዕታትና ስለ ክብረ በዓላት፣ ሰንበተ ክርስቲያን የዕረፍት ቀን ስለ መሆኗ፣ በሰሙነ ሕማማት የምእመናን ከተግባረ ሥጋ ማረፍ ግዴታ ስለ መሆኑ ይገልጻል፡፡

4. የመልዕክት ክፍል

የመልእክታት ክፍል መጽሐፍት ለግለሰቦች፣ ለቤተሰብ፣ ለቤተክርስቲያን ወይም ለማኅበር

የተጻፉ ሲሆን ነገረ ሃይማኖትና ተግሳጽን ሥነ ምግባርን ወዘተ የሚገልጹና የሚያስተምሩ መጻሕፍት ናቸው፡፡

የመልዕክታት ክፍል መጻሕፍት ቁጥራቸው 21 ሲሆን ጸሐፊዎቹ ግን የተለያዩ ናቸው፡፡ 14ቱ የቅዱስ ጳውሎስ፣ የጴጥሮስ ሁለት፣ የዮሐንስ ሦስት፣ የያእቆብ እና የይሁዳ አንድ አንድ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ መልዕክታቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተላኩና በእግዚአብሔር አነሣሽነት የተጻፉ ስለሆነ ከቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ቁጥር ውስጥ ይካተታሉ፡፡

የመልእክታት ክፍል መጻሕፍት አከፋፈል

- ለማህበር የተላኩ:- ለምሳሌ የሮሜ፣የፊሊጲስዩስ....
- ለግል የተባሉ:- የፊልሞና፣የጢሞቴዎስ....
- ለዓለም አቀፍ የተላኩ:- ለምሳሌ የዕብራውያን፣ 1ኛ ዮሐንስ መልዕክት ወዘተ ናቸው፡፡

1. የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክታት

የቅዱስ ጳውሎስ የቀድሞ ስም ሳውል ይባል ነበር ትርጉሙም የእግዚአብሔር ጥያቄ ማለት ነው፡፡ የተወለደው በኪልቅያ አውራጃ ጠርሴስ በሚባል ከተማ ሲሆን በሃይማኖቱ ፈሪሳዊ ከነገደ ብንያም የተወለደ ነው፡፡ (ሮሜ 11÷1) (ሐዋ 21÷39) ሮማዊ ዜግነትም ነበረው፡፡ (ሐዋ 9÷11)፣(ፊሊ 3÷5)

ወላጆቹ በልጅነቱ ገማልያል ለተባለ የሕግ መምህር ሰጡት፡፡ የአሪት ሕግ ከእርሱ ተምሯል፡፡ ከትምህርቱም በተጨማሪ የድንኳን የመስፋት ጥበበ ዕድ ተምሮ ራሱን ያስተዳድር ነበር፡፡ (ሐዋ 22÷3) ቅዱስ ጳውሎስ ለአባቶቹ ሕግ ቀናተኛ ስለነበረ ክርስቲያኖቹን ያሳድድ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም ያሉትን ክርስቲያኖች ለማሳደድ እየተጓዘ እያለ ከደማስቆ በር ሲደርስ እግዚአብሔር በድንቅ አጠራር ጠርቶት ምርጥ ዕቃን አድርጎት ወንጌልን የሚያስተምር አደረገው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ሦስት ሐዋርያዊ ጉዞዎች ያደረገ ሲሆን አስራ አራት ያህል መልዕክታትንም ጽፏል። ቅዱስ ጳውሎስ በቃል ካስተማረው ይልቅ በመልእክቱ ያስተማራቸው ብዙ ናቸው።

ሀ. ወደ ሮሜ ሰዎች

ሮም ከጥፋት ውኃ በፊት አስጣጣሊስ ትባል ነበር። ከዚያ በኃላ የከይተም ልጆች ሰፍረውባት ከይተም ተባለች። ቀጥሎም አንጣሎስ በተባለ ንጉሥ ስም አማካይነት ኢጣሊያ ተብላለች። በ735/730 ዓ.ም ደግሞ ሮሙላስ በተባለው መሪዋ ሮም ተብላለች። አሁን የኢጣሊያን ዋና ከተማ ስትሆን ቀደም ሲል የዓለም ከተማ ነበረች።

ቅዱስ ጳውሎስ የፃፈው ለሮማ ክርስቲያኖች በግሪክ (ቆሮንቶስ) በ54(56-57) ዓ.ም ሲሆን መልዕክቱ በቅድስት ፌቨን በኩል ተወስዷል።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ከአይሁድና ከአህዛብ በተመለሱ ክርስቲያኖች መካከል የተፈጠረው ጠብ ለማጥፋት
2. በሥጋ ለተሾሙ እንዲገዙ በነፍስ ግን ለክርስቶስ መገዛት እንዲገባ ለማስረዳት
3. ወደ ሮም ከመጓዙ በፊት እየተማሩ እንዲቆዩ

አከፋፈሉ፡- 16 ምእራፎች ሲኖሩት በ6 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. (ከምዕ 1÷1-17)፡- የመግቢያ ሰላምታ
2. (ከምዕ 1÷18-5÷21)፡- ስለአረማውያን፣ ስለአይሁድና ስለእግዚአብሔር ጽድቅ
3. (ከምዕ 6÷1-8÷9)፡- ሰው ከጻድቀ ከኃጢአትና ከሞት ኃይል ነፃ መሆኑን
4. (ከምዕ 9÷1-11÷36)፡- ስለ እስራኤል መመረጥና ተስፋ
5. (ከምዕ12÷1-15÷13)፡-የክርስቲያኖች አኗኗር በዓለም በግልና በቤተክርስቲያን
6. (ከምዕ 15÷14-16÷27)፡- መደምደሚያ

ለ. የመጀመሪያይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ቆሮንቶስ የአካይያ ሁለተኛ ከተማ ስትሆን በቅዱስ ጳውሎስ ዘመን 6 መቶ ሺህ ሰዎች የሚኖሩባት ከአቴና 75 ኪ.ሜ ርቃ የምትገኝ የግሪክ ከተማ ናት። ይህቺ ከተማ በባሕር መገናኛ ላይ የተመሠረተች ስመ ጥር እና ታላቅ በንግድ የታወቀች የሀብታሞች መናኸሪያ ነበረች። አፍሮዲጡ የሚባል ጣኦት የሚመለክባት፣ ዝሙት የሚሠራባት ከተማ ነበረች። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስ በሁለተኛ ጉዞው በ50 ዓ.ም አካባቢ አስተምሯል። የቆርንቶስ ቤተክርስቲያንንም መሥርቷል። በሦስተኛ ጉዞውም በኤፌሶን እያለ ልጁ ጢሞቴዎስን ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ይመለሱ ዘንድ ልኮላቸዋል።

ቅድስ ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በኤፍሶን ሳለ በ 54/55 ዓ.ም በቅዱስ ጢሞቴዎስ መልዕክት ወሳጅነት ነው።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. **እኔ የአጵሎስ፣እኔ የጳውሎስ፣እኔ የክርስቶስ ነኝ በማለት በመከፋፈላቸው ችግሩን ለመቅረፍ**
2. ከታወቁበት የዝሙት ኃጢአት እንዲመለሱ

3. የቆሮንቶስ ሴቶች በሥርዓት እንዲኖሩ ለመምከር
4. በጸጋ መቀናናታቸውን እንዲያቆሙ ለመግለጽ

አከፋፈሉ፡- 16 ምዕራፎች ሲኖሩት በ5 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል

1. (ከምዕ 1÷1-9)፡- መፅ.ጸ
2. (ከምዕ 1÷10-4÷21)፡- በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስላለው መለያየት
3. (ከምዕ 5÷1-6÷20)፡- ከዝሙት ርቀው በህግ □ንዲኖሩ
4. (ከምዕ 7÷1-15÷58)፡- ለጣዖት ስለተሠ□ ሥፉ እና በማኅበር ሲሰበሰቡ ሊያደርጉት ስለሚገባው ነገር
5. (ከምዕ 16÷1-24)፡- መ□ም□ሚጸ

ሐ. ሁለተኛይቱ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ቅዐ ስ ቭ□ሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በመቄዶንያ በ57 ዓ.ም ሲሆን መልዕክቱንም በቅዱስ ቲቶና በሉቃስ እፀ ልኮታል።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ንስሐ ገብተው በመመለሳቸው ለማመስገን የተደናገጡትን ደግሞ ለማረጋጋት
2. ከሐሰተኞች መምህራን □እንዲጠበቁ ለማስጠንቀቅ

አከፋፈሉ፡-13 ምዕራፎች ሲኖሩት በ4 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. (ከምዕ 1÷1-2÷11)፡- መፅ.ጸ
2. (ከምዕ 2÷12-7÷16)፡- □ቅዐ ስ ቭ□ሎስ እና የባልንጀሮቹ አገልግሎት በመከራ ውስጥ
3. (ከምዕ 8÷10-9÷15)፡- ስለ ልግስና አገልግሎታቸው ማበረታቻ
4. (ከምዕ 10÷1-13÷14)፡- ውሸተኞች ወንድሞችን በመ□ገላቸው የጻፈው ወቀሳ እና ማጠቃለጸ

መ. ወደ ገላትያ ሰዎች

ገላትያ በታናሿ □ስያ ትገኝ የነበረች አውራጃ ስትሆን ዛሬ የቱርክ መናገሻ ከተማ የሆነችው አንካራ የምትገኝበት አካባቢ ነው። ስያሜዋን ያገኘችውም ጉዋል የተባሉ ሕዝቦች ይኖሩበት ስለነበረ ነው። የገላትያ ቤተክርስቲያን ሐዋርያው ቅዱስ ቭ□ሎስ በ46 □ም ባ□ረቹ□ □መጸመሪጸ□ ሐ□ርጸዊ ቱዞ □መሠረታት ናት። በ54 ዓ.ም በሦስተኛ□ ቱዞ□ በፍርግያ አልፎ ገላትያ በመግባት በሃይማኖታቸው እንዲፀኑ አስተምሯቸው ሄዷል።

ቅዐ ስ ቭ□ሎስ መል□ክቱን የጻፈው ለገላትያ ክርስቲያኖች በሶርያ አንጾኪያ ሳለ በ48 ዓ.ም በቲቶ መልዕክት ወሳጅነት ነው።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. የአይሁድ መምህራንን የሐሰት ትምህርት እንዳይቀበሉ እና □ተማሩትን የሐዋርያት ትምህርት እንዲጠብቁ
2. የአይሁድ መምህራን እንደ ሌሎች ሐዋርያት ጌታን አላየም ከጌታም አልተማረም ከቅዱሳን ሐዋርያትም እኩል አይቆጠርም ይሉት ስለ ነበር ይህንን የእርሱን ሐዋርያነትና ሥልጣኑን ያውቁ ዘንድ

አከፋፈሉ፡-6 ምዕራፎች ሲኖሩት በአራት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. (ከምዕ 1÷1-10)፡- መፅቢጸ
2. (ከምዕ 1÷11-2÷21)፡- ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያነቱን ያረጋገጠበት ትምህርት
3. (ከምዕ 3÷1-4÷31)፡- ከኀጢያት ባርነት ነፃ ስለመሆናችን ስለ ሕግና ስለ ክርስቶስ
4. (ከምዕ 5÷1-6÷18)፡- ስለ ሰዎች የመልካም አኗኗር ሕይወት

ሠ. ወደ ኤፌሶን ሰዎች

ኤፌሶን በ□ናኗ □ስጸ በምዕራብ በኩል በኤጅያን ባህር አጠገብ ትገኝ የነበረች የወደብ ከተማ ነበረች፡፡ ከተማዋ ዛሬ በቱርክ ሃገር አያሰሎን የምትባል ከተማ ስትሆን ያን ጊዜ 350,000 ሰው የሚኖርባት ታላቅ የንግድ ከተማ ነበረች፡፡ በአርጤምስ (ቤተጣኦት) የታወቀች ናት፡፡
የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን የመሠረተው ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ጉዞው ለጥቂት ወራት በኤፌሶን ቆይቶ ነበር፡፡ በሁለተኛው ጉዞው በ50 ዓ.ም በኤፌሶን ከተማ ለሁለት ዓመት ከስድስት ወር አስተምሯል፡፡ ከከተማዋ በወጣ ጊዜም ጢሞቴዎስን ሊቀጳጳስ አድርጎ ሾሞላቸዋል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በ58 ዓ.ም የኤፌሶን ሰዎች በእምነት በምግባር መጽናታቸውን በመስማቱ በ□ቀመዌሙሩ በቲኪቆስ አማካኝነት መልዕክቱን ልኮላቸዋል፡፡ ይህች መልዕክት ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ታስሮ ሳለ ከጻፋቸው መልዕክት የመጀመሪያዋ ናት፡፡

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

የዓለም ሰዎች በምቀኝነት ለክርስቲያኖች የተለያየ ስም ያወጡላቸው ስለነበረ በክርስቶስ ክርስቲያን መባል ታላቅ መሆኑን ለማስረዳት

1. የዝሙትን አስከፊነት ለመግለጽ
2. ጋብቻ ታላቅና ቅዱስ እንደሆነ ለመግለጽ
3. አይሁድና አሕዛብ መለያየት ያበዙ ነበርና በክርስቶስ አንድ መሆናቸውን ለማስረዳት
4. ወደ ቀደመ ግብራቸው እንዳይመለሱ ዲያብሎስን እንዲቃወሙ ጻፈላቸው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ምክ 1)፡- መንፈሳዊ ሰላምና ምክር
2. (ከም 2-3)፡- ስለሰው ልጆች ዘላለማዊ ሕይወት
3. (ከምዕ 4-6)፡- ስለ ሥነ ምግባራዊ ትምህርቶች ያትታል፡፡

ረ. ወደ ፊሊጵስዩስ ሰዎች

ፊሊጵስዩስ የሰሜናዊ ግሪክ ክፍለ ሃገር የሆነችው የመቄዶንያ ዋና ከተማ የነበረች ሲሆን የቀድሞ ስሟ አሌኒደስ ትባል ነበር። በኃላ ግን የታላቁ እስክንድር አባት ፊልጶስ 2ኛ ግዛቷን አስፍቶ በስሙ ፊሊጵስዩስ አላት። የፊሊጵስዩስ ቤተክርስቲያን በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተመሰረተች ስትሆን በመጀመሪያው ጉዞው በከተማዋ አስተምሯል። የፊሊጵስዩስ ክርስትያኖች በመጀመሪያው የሮም እስራቱ በአፍሮዲጡ እፀ ስፈታ ልከውለታል፤ በ□ህም □ስ ተሰኝቷል። በዚህች ከተማ ልድያና የወኅኒ ቤቱ ጠባቂ አምነዋል።

ቅዐ ስ ቭ□ሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለፊሊጵስዩስ ክርስቲያኖች በሮም የመጀመሪያ እስራቱ በ60 □ም አካባቢ ሲሆን በደቀመዝሙሩ አፍሮዲጡ እና በቅዱስ ጢሞቴ- ስ አማካኝነት ልኮታል።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. **በአፍሮዲጡ አማ**ካኝነት ለላኩለት ስጦታ በመከራው የማይዘነጉትና በሃይማኖታቸው ጽኑ መሆናቸውን በማበረታታት የቀረበ ምስጋና
2. በመታሰሩ ምክንያት ላስቸገሩ ቢጽ ሐሳውያን መልስ ለመስጠት
3. በከተማዋ የነበሩት አይሁድ ‹‹እኛ የአብርሃም ዘር›› እያሉ ይመኩባቸው ነበርና እኔም እኮ የብንያም ዘር ነኝ በማለት መልስ ለመስጠት

አከፋፈሉ፡-

□ሐ□ርጸ□ **□ቅዐ ስ ቭ□ሎስ *መልዕክት* ወደ ፊሊ**ጵስዩስ ሰዎች 4 ምዕራፎች ሲኖሩት በአራት ክፍሎች ይከፈላል።

1. (ምዕ 1÷1-26)፡- መግቢያ
2. (ከምዕ 1÷27 - 2÷18)፡- ስለ ፊሊጵስዩስ ምዕመናን መንፈሳዊ ኑሮ
3. (ከምዕ 2÷19-3÷21)፡- ቅዱስ ጢሞቴዎስን እና አፍሮዲጡን እንደሚልክላቸው በተጨማሪም ከሐሰተኛ መምህራን እንዲጠበቁ
4. (ምዕ 4÷1-23)፡- ስለክርስቲያኖች ጽናት

ሰ. ወደ ቆላስያስ ሰዎች

ቆላስያስ በታናሿ እስያ ውስጥ በፍርግያ በስተደቡብ በሊከስ ወንዝ አጠገብ የተቆረቆረች የፍርግያ ዋና ከተማ ስትሆን አሁን ቱርክ ባለችበት ቦታ ትገኛለች። ከኤፌሶን 100 ማይሎች ያህል ትርቃለች። ቆላስያስ ከምዕራቡ ዓለም ወደ ምስራቅ በሚወስደው መንገድ ዳር ስለምትገኝ ዋና የንግድ ማዕከል ናት። በተጨማሪም በበግ ጸጉር ምርቷ ትታወቃለች። ወደዚህች ከተማ ገብቶ ወንጌልን በቅድሚያ የሰበከው ኤጳፍራስ የተባለው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ሲሆን ፊልሞናና አክርጳስም ሃገራቸው በመሆኑ ወንጌልን ሰብከውባታል።

ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለቆላስያስ ክርስቲያኖች በሮም የመጀመሪያ እስራቱ በ58 ዓ.ም አካባቢ ሲሆን በቲኪቆስ እና አጥሲምስ እጅ ልኮታል።

መልእክቱን **የተጻፈበት** ምክንያት፡-

1. ለግሪክና ለኤፌሶን ፈላስፎች መልስ የሚሆን የእግዚአብሔርን ማንነት የጌታችን አዳኝነት ለመግለጥ
2. ስለ ማኅበራዊ ኑሮ የመንፈሳዊ ሰው ጠባያትን ይዘረዝራል

አከፋፈሉ፡-የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆላስይስ ሰዎች 4 ምዕራፎች ሲኖሩት በ3 ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. (ምዕ 1÷1-14)፡- መግቢያ
2. (ከምዕ 1÷15 - 2÷23)፡- ስለ ክርስቶስ ፈጣሪነትና ሰው መሆን በተጨማሪም ስለሐዋርያት ታላቅነት
3. (ከምዕ 3÷1 - 4÷18)፡- ስለ ክርስቲያናዊ ኑሮ

ሸ. የመጀመሪያይቱ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

ተሰሎንቄ የመቄዶንያ ዋና የወደብ ከተማ ነበረች፡፡ የቀድሞ ስሟም ቴርማ ይባል ነበር፡፡ ትርጉሙም ፍልውሃ ማለት ነው፡፡ ይኸውም አጠገቧ ከነበረው የፍልውሃ የተወሰደ ነበር፡፡ በኋላ ግን ከሳንደር የተባለ ገዥ የታላቁን እስክንድር እህት ሰሎኒቃን ስላገባ ከተማዋን በስሟ አደረገው፡፡ ተሰሎንቄ ዛሬ የግሪክ ግዛት ናት፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛው ሐዋርያዊ ጉዞ ወቅት ከሲላስና ጢሞቴዎስ ጋር መጥቶ ለ3 ሣምንት አስተምሯል፡፡ ነገር ግን በምኩራብ ሲያስተምር ኦሪታችንን ሊያሳልፍብን ነው በሚል ፍርሃት ተነሣስተው አይሁድ ስለተቃወሙት ከተማዋን ለቆ ወደ ቤርያ አመራ፡፡ በዚያ ያሉት አይሁድ ትምህርቱን በሚገባ በመከታተላቸው የተበሳጩትን የተሰሎንቄ አይሁድ ስለተቃወሙት ወደ አቴና አመራ፡፡ ከአቴና ወደ ቆሮንቶስ ሲገባ ከሲላስና ጢሞቴዎስ ጋር ተገናኘ፡፡

የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የተፃፈው ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በአቴና ከተማ ሲሆን በ50 ዓ.ም በቅዱስ ስልዋኖስ (ሲላስ) እና ጢሞቲዎስ እጅ ልኮላቸዋል፡፡

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. የተሰሎንቄ ክርስቲያኖችን ለማጽናናት
2. የተሰሎንቄ ምዕመናን መከራከር ያበዙ ስለነበር የተማሩትን ትምህርትና ሃይማኖት መጠበቅ እንጂ ክርክርን እንዳያበዙ ጻፈላቸው
3. በአጠቃላይ ፍጹማኑን የበለጠ ለማበረታታት ተከፍሎ ልብ ያላቸውን ለማጽናት አንዳንዶችንም ለመገሰጽ ጽፎላቸዋል፡፡

አከፋፈሉ፡-5 ምዕራፎች ሲኖሩት በሁለት ይከፈላል፡፡

1. (ከምዕ 1÷1-3÷13)፡- ስለተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን
2. (ከምዕ 4÷1-5÷28)፡- ስለ ቅድስና፣ ዳግም ምጽአትና የምዕመናን የጎበረት ኑሮ

ቀ. ሁለተኛይቱ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን የጻፈው ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በሎዶቅያ በ51 ዓ.ም ሲሆን በጢሞቲዎስ እና በሲላስ እጅ ልኮላቸዋል፡

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

ዳግም ምጽአት በቅዱስ ጳውሎስ ዘመን ይደረጋል በማለት ያሸበሩ መናፍቃን በመኖሣታቸው፣የተሰሎንቄ ክርስቲያኖች በጥርጥርና በፍርሃት በመዋጣቸው፡፡

አከፋፈሉ፡-ሦስት ምዕራፎች ሲኖሩት በ3 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. (ምዕ 1÷1-12)፡- ክርስቲያንና መከራው
2. (ምዕ 2÷1-17)፡- ስለዳግም ምጽአት
3. (ምዕ 3÷1-18)፡- ሥራ እንዲሰሩና እንዲጸልዩ ምክር

በ. የመጀመርያይቱ ወደ ጢሞቴዎስ

ጢሞቴዎስ የልስጥራ ሰው ሲሆን ልስጥራ ደግሞ በዛሬይቱ ደቡባዊ ቱርክ ውስጥ የምትገኝ ነች፡፡ ጢሞቴዎስ ማለት ዘአልቦ ጥሪት (ምንም የሌለው) ማለት ሲሆን ቅዱስ ጳውሎስ በሃይማኖትና በትምህርቱ የወለደው የበኩር ልጁ ነው፡፡ ቅዱስ ጢሞቴዎስ በዕድሜ ወጣት የሆነ በሃይማኖትና በምግባር የጸና በመሆኑ ቅዱስ ጳውሎስ ድቁናን ሰጠው፡፡ ለብዙ ጊዜያትም እየተላከ ካገለገለ በኋላ ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ቤተክርስቲያን ጳጳስ አድርጎ ሾሞታል፡፡ አንድ ጊዜ መታሰሩም ይነገራል፡፡ ሐዋርያዊ ተልእኮውን እየፈጸመ እያለ በ96 ዓ.ም አካባቢ በሰማዕትነት አርፏል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን የፃፈው ለመንፈስ ልጁ ጢሞቴዎስ በ60 ዓ.ም አካባቢ በሎዶቅያ የሁለት ዓመት የቁም እስሩን በጨረሰ ጊዜ ነው፡፡ መልእክቱንም በቲቶ እጅ ልኮለታል፡፡

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ከዚህ ቀደም ስለ ሥርዓተ ኖሎት (ክህነት) ያልጻፈ ስለነበር በዚህ ምክንያት ጻፈለት
2. በኤፌሶንና አካባቢዋ ለተስፋፋው የግኖስቲኮች ፍልስፍና ክርስቲያናዊ ምላሽ ለመስጠት
3. ጢሞቴዎስን ለማረታታት ወጣትነቱን ተመልክቶ ማንም እንዳይንቀው

አከፋፈሉ፡-1ኛ ጢሞቲዎስ 6 ምዕራፎች ሲኖሩት በ3ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. (ምዕ 1÷1 - 3)፡- መግቢያ
2. (ከምዕ 1÷3-6÷19)፡- ስለ ቤቱ-ክርስቲያን አስተዳደር የተጻፈ ትምህርተ ኖሎት
3. (ምዕ 6÷19-21)፡- ለቅዱስ ጢሞቴዎስ የተሰጠው አደራ እና ማጠቃለያ

ተ. ሁለተኛይቱ ወደ ጢሞቴዎስ

ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለቅዱስ ጢሞቴዎስ በ66 ዓ.ም በሁለተኛው እስራቱ በሮም ወህኒ ቤት ሳለ ሲሆን በቅዱስ አንክሮሎስ አማካኝነት ልኮለታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን በጻፈበት ወቅት የ74 ዓመት አዛውንት ነበረ፡፡ ከአንድ ዓመት በላይ በጨለማ እስር ቤት በመኖሩ ዓይኖቹ ከመድከማቸው ተጨማሪ የመሞቻው ጊዜ እየተቃረበ መሆኑን

ያውቅ ነበር። መልዕክቱን ከጻፈ በኋላ በሕይወት የቆየው ለአንድ ዓመት ከ3 ወር ያህል ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ በሰማዕትነት አርፏል። ይህ መልዕክትም ከመልዕክቶቹ የመጨረሻዋ ናት።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ከሐሰተኞች መምህራን ሕዝቡን እንዲጠብቅ ለማሳሰብና ለመሞከር
2. ለጢሞቴዎስ የመሰነባበቻ መልእክት ይሆን ዘንድ ፅፎለታል።

አከፋፈሉ፡-አራት ምእራፎች ሲኖሩት በሦስት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. (ምዕ 1÷1-18)፡- መግቢያ እና ሰላምታ
2. (ከምዕ 2÷1 - 3÷17)፡- ስለ ቤተክርስቲያን፣ ስለሚመጣው አስጨናቂ ዘመን እና የአገልግሎት ትምህርት
3. (ምዕ 4÷1-22)፡- ማጠቃለያ

ቸ. ወደ ቲቶ

ቲቶ ትውልዱ አረማዊ ሲሆን የአንጾኪያ ሰው ነው። የስሙ ትርጓሜም ሠርቅ ማለት ነው። በቅዱስ ጳውሎስ ስብከት ሰላመነ በሃይማኖት የወለደው ልጅ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቲቶን የቀርጤስ ሊቀ ጳጳስ አድርጎ ሾሞት ነበር። ቀርጤስ በሜዴትራንያን ባሕር የምትገኝ ደሴት ስትሆን ብዙ አይሁድ ይኖሩባት ነበር። ከእነዚህም መካከል በበዓለ ሃምሳ የቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት አምነው የተጠመቁ ነበሩ። ቅዱስ ጳውሎስ ከሁለት ዓመት የቁም እስር ሲለቀቅ ወደ ደሴቲቱ ገብቶ አስተምሯል።

ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለቅዱስ ቲቶ በ63 ዓ.ም በሂቆጵልዮን ሲሆን አርጣ በተባለው ደቀመዝሙሩ አማካኝነት ልኮለታል።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ቀሳውስትንና ጳጳሳትን የሚሾምበትን መመዘኛ ለማሳወቅ
2. ሕዝቡን የሚመራበትን ሥርዓት ለመግለጽ

አከፈፋሉ፡-ሦስት ምዕራፎች ሲኖሩት በሁለት ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል

1. ስለቀሳውስት አሿሿም እና ስለ ሐሰተኛ መምህራን (11÷16)
2. ስለ ቤተ-ክርስቲያን መሪዎች አርአያነት (2÷1 - 3÷16)

ኀ. ወደ ፊልሞና

ፊልሞና ማለት ስውር ቦታ ማለት ሲሆን ሀገሩ ቆላስይስ የሆነ ደግ ባለጸጋ ነበር። በቤቱ ከርስቲያኖችን እየሰበሰበ ያበላ ያጠጣ ነበር። ወደ ኤፌሶን ለስራ በሄደ ጊዜ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር በመገናኘቱ ከነቤተሰቡ አምኖ ተጠምቋል። ከኤፌሶን ወደ ቆላስይስ ተመልሶ አናሲሞስ የተባለ አገልጋይ ነበረው። ይህ አገልጋይ የሚጠብቃቸው ከብቶች ጠፍተውበት ወደ ሮሜ በኮበለለ ጊዜ የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ሰምቶ አምኖ ተጠመቀ። የመጣበትንም ሁኔታ ለቅዱስ ጳውሎስ ነገረው።

ቅዱስ ጳውሎስ መልዕክቱን የጻፈው ለፊልሞና እና ለሚስቱ ለአፋብያ እንዲሁም ለልጁ ለአክርጳስ በ60 ዓ.ም አካባቢ በሮም የመጀመሪያ እስራቱ ወቅት ሲሆን በአናሲሞስ አማካኝነት ልኮታል።

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. አናሲሞስን ከፊልሞና ለማስታረቅ
2. በስብከተ ወንጌል አገልግሎት የተጠመቁትንም በማጽናት እንዲበረቱ ጽፎታል።

አከፋፈሉ፡-አንድ ምዕራፍ 25 ቁጥሮች ሲኖሩት በ2 ይከፈላል

1. (ከምዕ 1 - 7)፡- መግቢያ እና ሰላምታ
2. (ከምዕ 8 - 25)፡- ስለአናሲሞስ የቀረበ ምልጃ እና ማጠቃለያ

ነ. ወደ ዕብራውያን ሰዎች

ዕብራውያን /አብርሃም ቅድመ አያት/ በአባታቸው በሜቦር ዕብራውያን የተባሉ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ የአይሁድ ምዕመናን ናቸው። ይህ መልዕክት የተጻፈው ሮማውያን የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ካፈረሱበት ከ70 ዓመት በፊት ነው። መልዕክቱ በአዲስ ኪዳን ዘርን ወይም ዜግነትን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ ስለሚገኝ ጸጋ ያስረዳል።

ቅዱስ ጳውሎስ ይህችን መልዕክት በኢየሩሳሌም፣በኢጣሊያና በእስክንድርያ ለሚኖሩ ከአይሁድ ወደ ክርስትና ለተመለሱ ክርስቲያኖች በ60 ዓ.ም በደቀመዝሙሩ ጢሞቴዎስ አማካኝነት ልኮላቸዋል።

በዚህች መልእክት ላይ እንደሌሎቹ የጸሐፊው ስም ባለመጠቀሱ የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት አይደለም የሚሉ አይታጡም። ነገር ግን የቁስጥንጥንያው ሊቀጳጳስ ዮሐንስ አፈወርቅ የጳውሎስ መልዕክት መሆኑን አስረድቷል። (ዜና ሐዋርያት ገጽ 250) ሌሎች የቤተ ክርስቲያን አበው ሊቃውንትም በመልዕክቱ መጨረሻ ላይ የደቀመዝሙሩ የጢሞቴዎስ ስም መጠቀሱን መነሻ በማድረግ መልዕክቱ የቅዱስ ጳውሎስ መሆኑን ያስረዳሉ። (ዕብ 13÷23)

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መምጣት ትንቢት የተነገረለት ሱባዔ የተቆጠረለት መሆኑን ለመግለጽ
2. ኢየሱስ ክርስቶስ ከነቢያት፣ ከካህናትና ከመላእክት እንደሚበልጥ ለማስረዳት
3. በኦሪት ሕግ ብቻ ይኖሩ የነበሩ አይሁድ ወደ ክርስትና እንዲመለሱ ጽፎላቸዋል።

አከፋፈሉ፡-13 ምእራፎች ሲኖሩት በ3 ዓበይት ክፍሎች ይከፈላል።

1. (ከምዕ 1÷1-7÷28)፡- የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት፣ የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጅነትና ከነቢያት እና ከብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ስለ (ከምዕ 8÷1-10÷18)፡- አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን የላቀ ስለመሆኑ
2. መብለጡ
3. (ከምዕ 10÷19-13÷25)፡- ስለክርስትና ሕይወት

2 ሰባቱ መልዕክታት

ሰባቱ መልዕክታት ተብለው የሚታወቁት የቅዱስ ጴጥሮስ 1ኛ እና 2ኛ፣ የቅዱስ ያዕቆብ፣ የቅዱስ ዮሐንስ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ መልዕክቶች ናቸው። ሰባቱ መልዕክታት የተባሉትም ምክንያት ለአንድ ግለሰብ ወይም ለአንድ ቤተክርስቲያን የተጻፉ ሳይሆን ለመላው አብያተ ክርስቲያናት ስብስቦች የተላኩ መልእክታት በመሆናቸው ነው።

የቅዱስ ጴጥሮስ መልዕክታት

የቀድሞ ስሙ ስምዖን ይባል ነበር እናቱ በነገደ ስም ስምዖን ብላ እንዳወጣችለት ይነገራል። ጴጥሮስ የሚለውን ያወጣለት ጌታችን ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ የሐዋርያት አለቃ ቁጥሩም ከአዕማድ ሐዋርያት መካከል ሲሆን ከሐዋርያት በዕድሜ አንጋፋውም እርሱ ነው ለደቀመዛሙርትነት ሲጠራ ዕድሜው 55 ነበር።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የጻፋቸው መልዕክታት በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ሁለት ናቸው። እነርሱም

ሀ. የመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የቅዱስ የጴጥሮስ መልዕክት

በሰማዕቱ እስጢፋኖስ ላይ በ35 ዓ.ም አካባቢ በደረሰው መከራ ተሳቀው ብዙ ክርስቲያኖች ተሰደው ነበር። ቅዱስ ጴጥሮስም

እንደ አባትነቱ ባሉበት ሆነው በእምነታቸው እንዲጸኑ በስልዋኖስ እጅ ሮም (ባቢሎን) ውስጥ በ60 ዓ.ም ጽፎ እንደላከ ይነገራል።(1ኛ ጴጥ 5÷12)

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. መከራና ችግርን እንዲታገሱ ለመምከር
2. የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው እንዲያውቁ
3. ከሥጋ ምኞት እንዲጠበቁ
4. ከሁሉ ጋር ባላቸው የሚገባ ግንኙነት ትሁታን እንዲሆኑ

አከፋፈሉ፡-

1. (ምዕ 1÷1-2)፡- መንፈሳዊ ሰላምታ
2. (ከምዕ 1÷3-12)፡- መከራን ስለመቀበል እና ስለሚዘጋጀው መዳን
3. (ከምዕ 1÷13 - 2÷22)፡- ስለ ተጠራንለት ቅድስና
4. (ምዕ 3)፡- ሰው ከክፉ ነገር መራቅ እንዳለበት
5. (ምዕ 4)፡- በመከራ ወቅት ደስታ ስለመኖሩ
6. (ምዕ 5)፡- ለቤተክርስቲያን ካህናትና አባላት የተሰጠ ማጽናናትና የሚገባ ማኅበራዊ ትጋት

ለ. ሁለተኛይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ መልዕክት

ቅዱስ ጴጥሮስ በኔሮን አዋጅ ተይዞ በእስራት ሳለ በ67 ዓ.ም አካባቢ መናፍቃን የክህደት ትምህርት እያስተማሩ ክርስቲያኖችን አውከዋቸው ነበርና ለታናሿ እስያ አካባቢ ላሉ ምእመናን ይህን መልዕክት ጽፎላቸዋል፡፡

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ለዚህ ዓለም ሠራዔ መጋቢ የለውም
2. ትንሣኤ ሙታን የለም
3. ኅልፈተ ሰማይ ወምድር የለም
4. አንድ ጊዜ ካመኑ ምግባር አይጠይቅም በማለት መናፍቃን ላነሷቸው ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ምዕ 1÷1-21)፡- ስለ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር
2. (ምዕ 2÷1-22)፡- ስለ ሐሰተኛ መምህራን
3. (ምዕ 8÷1-8)፡- ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያትታል፡፡

፲.ሉየቅዱስ ዮሐንስ መልእክታት

ሐ. የመጀመሪያይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ መልዕክት

ቅዱስ ዮሐንስ በ96 ዓ.ም አካባቢ በድምጥያኖስ ቄሳር በፍጥሞ ደሴት ታስሮ ከተፈታ በኋላ በእስያ አውራጃ ለነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የመጀመሪያው መልዕክት ጽፏል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ በድምጥያኖስ ትዕዛዝ መታሰሩን ያዩ መናፍቃን ፡-

1. ትንሳኤ ሙታን የለም
2. በነቢብ እና በገቢር እንጂ በኃልዮ የምንሠራውን ኃጢአት እግዚአብሔር አያውቀውም
3. ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ አልተገለጠም
4. ከጥምቀት በኋላ ምግባር መሥራት ጥቅም የለውም እያሉ የክህደት ትምህርታቸውን በማስተማራቸው ለእነርሱ ምላሽ ለመስጠት ሲል ይህን መልዕክት ጽፎላቸዋል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ምዕ 1÷1-4)፡- ስላየውና ስለሰማው የክርስቶስ መገለጥ
2. (ምዕ 1÷5 - 2÷17)፡- በምግባር በሃይማኖት መጽናናት እንዳለባቸው
3. (ምዕ 2÷18-29)፡- ስለሚነሡት የክርስቶስ ተቃዋሚዎች
4. (ምዕ 3÷1-4÷6)፡- ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ልጆች ስለመሆናቸው
5. (ምዕ 4÷7-5÷5)፡- እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ፍቅርና ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንዲዋደዱ
6. (ምዕ 5÷6-21)፡- ስለክርስቶስ እውነተኛ አምላክነት እና ዘላለማዊ ሕይወት

መ. ሁለተኛይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ መልዕክት

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ይህን መልእክት በኤፌሶን ከተማ በ96 ዓ.ም አካባቢ ለአንዲት በኤጂያን ደሴት አካባቢ ቀለብ እየተሰፈረለት የንግሥቲቷን ልጆች ለምታሳድግ ሮምና ለተባለች ሴት እና ለቤተሰቦቿ ጽፎታል፡፡

ቅዱስ ዮሐንስና ደቀመዝሙሩ አብሮኮሮስ አስተምረው አሳምነው አጥምቀው ወደ ክርስትና ከመለሷት በኋላ ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ሲታሰር መናፍቃን የክህደት ትምህርታቸውን በማስነሣታቸው የክርስቲያኖች ጉባዔ መከፋፈል ደርሶበት ጸብ ክርክር ተነሣ፡፡ ይህን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስ የድሮ ሕይወቷን አስታውሳ ይህን መከራ እንድትረሳ እመቤት እያለ በመጥራት ይህን መልዕክት ጽፎላታል፡፡

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት

በመጀመሪያው መልእክቱ መናፍቃን ምዕመናንን ለማስኬድ ይጣደፉ ስለነበረ የሐሰት ትምህርታቸውን በመቃወም በእውነተኛው ትምህርት እንዲጸኑ ነው፡፡ ይህችንም መልእክት ምዕመናን በተሰባሰቡበት ያነቧትና በቅጂው ለሌሎች ያስተላልፉ ነበር፡፡ ምክንያቱም የመጀመሪያው መልእክት ጭምር በማጠቃለል ከመናፍቃን መጠበቅ እንዳለባቸው ታስረዳለችና፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከቁ 1-3)፡- መንፈሳዊ ሰላምታ
2. (ከቁ 4-6)፡- የምእመናን አንድነትና ጸንቶ የመኖር ትምህርት
3. (ቁ 7-11)፡- የሐሰተኞችን ትምህርት ስለመቃወም
4. (ከቁ 12-13)፡- ብዙ ያልተጻፈ ስለመኖሩ እና ለሰዎች የሚቀርብ ሰላምታ

ሠ. ሦስተኛይቱ የሐዋርያው የቅዱስ ዮሐንስ መልዕክት

ይህን መልዕክት ቅዱስ ዮሐንስ ጋይዮስ ለተባለ ሰው በ96 ዓ.ም ልኮለታል፡፡ ጋይዮስ ስሙ (በሮሜ 16፥23) ላይ የተጠቀሰ ሲሆን እንደ አብርሃም እንግዳ የሚቀበል ደግ ሰው እንደነበረ ይነገራል፡፡ ይህን ደግነቱን የሰማው ቅዱስ ዮሐንስ ስለ ደግነቱ፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪነት እያበረታታ እያመሰገነ ጽፎላታል፡፡

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ጋይዮስን ለማመስገን
2. በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ መለያየት እንዳይኖር ስለመምከር
3. ዲዮጥራጢስን ለመገሠጽ ጽፏል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከቁ 1-4)፡- ለጋይዮስ ስለ እምነቱ ጠንካራነት የቀረበ ምስጋና
2. (ከቁ 5-8)፡- ለጋይዮስ ስለ እንግዳ ተቀባይነቱ የቀረበ ምስጋና
3. (ከቁ 9-11)፡- በዲዮጥራጢስ ላይ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ
4. (ከቁ 12-14)፡- ስለ ዲሜጥሮስ የተሰጠ ምስክርነት
5. (ቁ15)፡- ለጋይዮስና ለወገኖቹ የቀረበ ሰላምታ

ረ. የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብ መልዕክት

በሐዲስ ኪዳን የጌታ ወንድም፣ ወልደ እልፍዮስ፣ ታናሹ ያዕቆብ በመባል ይጠራል። ጸሎት ወዳድ በመሆኑ እግሩ ያብጥበት ስለነበረ በኢየሩሳሌም ኢጲስቆጶስነት ተሹሞ ያገለግል ነበር።

የጌታ ወንድም እየተባለ የሚጠራው የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ተበታትነው ለነበሩ ከአይሁድነት ወደ ክርስትና ለተመለሱት በ50 ዓ.ም አካባቢ ይህችን መልዕክት ጽፎላቸዋል። መልእክቱ ‹‹የፍቅርና የትህትና መልእክት›› ትባላለች ምክንያቱም ከአሥራ ሦስት ጊዜ በላይ ወንድሞች ሆይ እያለ በትህትና ይጽፋልና።

መልእክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. በስደት ላይ ስለነበሩ እነርሱን ለማበረታታትና ለማጽናት
2. በመከራውና በስደቱ ተስፋ እንዳይቆርጡ፣ ክብር ዋጋ እንዳላቸው ለመግለጽ
3. በቅዱስ ጳውሎስ የተጻፈውን የነገረ ሃይማኖት ትምህርት እንዲያጸኑ እንዲሁም ምግባር አስፈላጊ መሆኑን ለመግለጽ ሲል ጽፎላቸዋል።

አከፋፈሉ፡-

1. (ምዕ 1፥1-18)፡- ስለ በእምነት መፈተን እና የፈተና መንስኤ
2. (ምዕ 1፥19-3፥18)፡- አጠቃላይ ትምህርቶች
3. (ምዕ 4፥1-5፥20)፡- ልዩ ልዩ ምክሮች

ሰ. የሐዋርያው የቅዱስ ይሁዳ መልዕክት

በሐዋርያት ዝርዝር፣ በማቴዎና በማርቆስ ወንጌል ታዴዎስ/ልብድዮስ/ ብለው ሲጠሩት በሉቃስ ‹‹የያእቆብ ወንድም ይሁዳ›› በሐዋርያነት ሥራ ደግሞ ‹‹የያእቆብ ልጅ ይሁዳ›› ይለዋል። ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል አንዱ ነው።

ሐዋርያው ይሁዳ ይህን መልእክት በ65 ዓ.ም አካባቢ በግኖስቲኮች ትምህርት ግራ ተጋብተው ለነበሩ ለታናሿ እስያና ለመካከለኛው ምስራቅ ክርስቲያኖች ጽፎላቸዋል።

መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. ከግኖስቲኮች ትምህርት ርቀው የቀናውን ትምህርት እንዲይዙ ለማድረግ
2. ተመክረው ያልሰሙ እንደሚቀጡ የሚመለሱ ሰዎች ግን እንደሚጸኑ ለመግለጽ

አከፋፈል፡-

1. (ከቁ 1-16)፡- ስለ ሐሰተኛ ትምህርት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ
2. (ከቁ 17-26)፡- በእምነታቸው እንዲጸኑ የቀረበ ጥሪ

5 የትንቢት ክፍል

የቅዱስ ዮሐንስ ራዕይ

ይህ መጽሐፍ በግሪክ ቋንቋ ‹‹አቡቃለምሲስ›› በመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ዘንድ ደግሞ ‹‹የሐዲስ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍ›› ይባላል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ይህን ራዕይ በዘመነ ድምጥያኖስ ጊዜ ወደ ኤጅያን ባህር ወደ ፍጥሞ ደሴት በተያዘ ጊዜ ጽፎታል፡፡ ዛሬ በዚህች ደሴት ላይ ዮሐንስ ራዕይ ያየበትና የጻፈበት ዋሻ ትገኛለች፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ለሰባት ዓመት ያህል በግዞት ተቀምጦ ራዕዩን ባየበት ጊዜ ‹‹እንዲህ ብለህ ጻፍ›› አለኝ፡፡ እያለ ራዕዩን ጽፏል፡፡ በዚያ ደሴት ሳለ እንደወንድሞቹ እየተሠዉረ ባለማስተማሩ ሁልጊዜ ይተክዝ ስለነበረ እግዚአብሔር የበለጠውን ምስጢር ገልጦለታል፡፡

የዮሐንስ ራዕይ የተጻፈው በዚያ ዘመን ዮናናውያን ተብለው በሚጠሩት ሰባት የታናሿ እስያ ከተሞች ለሾማቸው ሊቃነ ጳጳሳት ነው፡፡ መላእክትም (አለቆችም) የተባሉት እነርሱ ናቸው፡፡ መጽሐፉ ወደ 300 የሚጠጉ ምሳሌዎችን የያዘ ሲሆን ስለ ሰማያዊ ሕይወት፣ የጻድቃንን፣ የሰማዕታትን ክብር እና ስለ መጪው ዘመን የሚያወራ ነው፡፡

ራዕየ ዮሐንስ የተጻፈበት ምክንያት፡-

1. መላእክት (አለቆች) ተብለው ለተጠሩት ሊቃነጳጳሳት በቤተክርስቲያን መልካም አስተዳደርና ሕይወት ዙሪያ ምክር ለመስጠት
2. የክርስቲያኖች ሰማያዊ ሕይወትና የቅዱሳንን ክብር ለማሳየት
3. የጥጦስን፣ የሐሳዊ መሲህን፣ የምጽአትን፣ የኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ነገር ለማስረዳት ተጽፏል፡፡

አከፋፈሉ፡-

1. (ከምዕ 1-3)፡- ለሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት የተጻፉ መልዕክቶች
2. (ከምዕ 4-5)፡- በሰማያት ስለሚደረገው የመጀመሪያ ገለጻ
3. (ከምዕ 6-11)፡- ስለ ሰባቱ ማኅተሞች እና መልእክቶች
4. (ከምዕ 12-13)፡- ስለ አውሬውና ሐሰተኛ ነቢያት
5. (ከምዕ 14)፡- በሰማያት ስለሚደረገው ነገር ሁለተኛ ገለጻ
6. (ከምዕ 15-16)፡- ስለ ሰባቱ ጽዋዎች
7. (ከምዕ 17-19)፡- ስለ ባቢሎን መፍረስ
8. (ከምዕ 20-22)፡- ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስረዳል፡፡

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

በብርሃናተ ዓለም ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤ/ክን ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት

ትምህርት ክፍልና ሐዋርያዊ አገልግሎት ክፍል የተዘጋጀ

መስከረም 2006 ዓ.ም